መጽሐፈ ኩፋሌ

*

በአንድምታ ትርጓሜ

አሳታሚ ፦-

ትንሣኤ ማሳተሚያ ድርጅት

፳፻ወሯ ዓ.ም.
አዲስ አበባ



ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ማትያስ ቀዳማዊ፣

ፓትርያርክ፣ ርዕሰ ሊቃነ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ

ሊቀ ጳጳስ ዘአክሱም፣ ወዕጨጌ ዘመንበረ ተክለ ሃይማኖት፣

መ ግ ሰ ጫ

መጽሐፈ ኩፋሌ :-

"ስሉንኬ ሕገጋት (መዳሕፍት) ዘስዘዝናክሙ"

በስምነታችሁ ስንድትጸኑባቸው ያዘዝናችሁ መዳሕፍት ስነዚህ ናቸው፤ በማለት ሦስት መቶው ሰሥራ ሰምንቱ ሰበው መምህራነ ቤተ ክርስቲያን የቅዱሳት መዳሕፍትን ቁጥር መጥነውና ወሰነው ሰቅድስት ቤተ ክርስቲያን ሰቆይተዋል::

ድንጋጌያቸውም:- **"ዘስዙዝ ተወክፎትን ኅበ ቤተ ክርስቲያን ቅድስት ዘኅልቆሙ ፹ወ፩ "** በቅድስት ቤተ ክርስቲያን ሲቀበሷቸው የታዘዙ ቁጥራቸው ፹፩ የሆነ ሰምሳካውያት መዳሕፍት በማለት የተገለጹት ናቸው::

"መዳሕፍት ሰምሳካውያት፣ ስስትንፋሰ ስግዚሰብሔር ነዮን" ሰምሳካውያት ቅዱሳት መዳሕፍት የስግዚሰብሔር ስስትንፋሶች ናቸው በማለት የማረጋገጫ ቃሳቸውንም ሰስፍረዋል:: (ፍት.ነ.ሰንቀጽ ፪፤፲፱)

በመሆኑም የ፹ወ፩ ቅዱሳት መዳሕፍት ሰካል የሆነው ሰንዱ መጽሐፈ ኩፋሌ የተሰኘው ነው::

ስንደ ሲቃውንተ ቤተ ክርስቲያን ሰገሳለጽ ስና ሰተረጓጉም መጽሐፈ ኩፋሌ ማለት **"ዝተከፍለ ስምሶሪት"** ማለት ሲሆን ከሰምስቱ መዳሕፍተ ሙሴ የተከፈለ፣ የዘመናትን ክፍል የሚናገር፣ ሰምስት ሺህ ሰምስት መቶውን ዘመን በሲዮቤልዩ የሚቆጥር መጽሐፍ ነው:: (ኪዳነ ወልድ ክፍሌ መጽሐፈ ሰዋሰው ወግሰ፣ ወመዝገበ ቃሳት ሐዲሰ፤ ገጽ ፻ሣ፫) የመጽሐፉም ጸሐፊ ሲቀ ነቢያት ሙሴ ነው::

ይህ በዚህ ስንዳስ ሰገራችን ሲትዮጵያ መዳሕፍተ ብሉያትን ከምንጫቸው መቀበሷ በታሪክ ሲወሳ፣ ሲነገርም ይኖራል:: በተግባርም ተተርጉሞስል :: "ሲትዮጵያ

እጆችዋን ወደ እግዚአብሔር ተዘረጋለች" (መዝ. ፳፯ ፤ ፴፩) ተብሎ የመንፈስ ቅዱስ ምስክርነት የተሰጠላት እናት አገራችን በብሉይ ኪዳን ሕገ ኦሪት ፣ በሐዲስ ኪዳን ሕገ ወንጌል ተሰብኮላታል፡፡ ለትምህርት፣ ለሥርዓት ፣ ለታሪክና ለሕግ ምንጭ የሆኗት የብሉያትና የሐዲሳት መጻሕፍት ኑፋቄ በዓለም ከመዘራቱ አስቀድሞ የገቡላትና የተቀበለቻቸው በመሆኑ ትምህርቷም ሆነ እምነቷ በጌታችንና በመድኃኒታችን በኢየሱስ ክርስቶስ፣ በነቢያትና በሐዋርያት መሠረት ላይ የጸና ነው፡፡

ይሁን እንጂ የመጻሕፍተ ብሉያት ምሥጢራዊ ትርጓሜ በግእዝና በአማርኛ በቤተ ክርስቲያን ሲቃውንት ተመርሖ ልቡና ተተርጉሞ ቃል በቃልና በእጅ ጽሑፍ ተጠብቆ እስከ እኛ ደርሶአል፡፡

ዛሬ ግን የመጻሕፍቱ ማለትም የብሉያቱ ምሥጢራዊ ትርጓሜ የእጅ ጽሑፍ የታሰካ ነገሥት በአታ ለማርያም የብሉያት መጻሕፍት ትርጓሜ ሲቅ የነበረት መጋቤ ምሥጢር ጌራ ወርቅ ጥበቡ ያስተምረበት የነበረው የብሉያት ትርጓሜ ቅዱሳት መጻሕፍት በቅደም ተከተል ታትመው በመሰራጨት ላይ መሆናቸው የሚታወስ ነው፡፡

ስለሆነም ይህ የመጽሐፈ ኩፋሌ ትርጉም በሲቃውንት ጉባሌ ታይቶና ተመርምሮ ታትሞ ለመምህራንና ለደቀ መዛሙርት እንደዚሁም ለመፍቀርያነ ቅዱሳት መጻሕፍት እንዲደርስ ለማድረግ በመቻላችን የታሰበውን የሚያስጀምር፣ የተጀመረውን የሚያስፈጽም ልዑል እግዚአብሔርን ከልብ እናመሰግናለን፡፡

ስብሐት ለእግዚአብሔር ለዘአብጽሐነ እስከዛቲ ሰዓት

ትንሣሌ ማሳተሚያ ድርጅት

፳፻ወ፭ ዓ.ም.



የብሉያት ትርጓሜና የቅኔ አብነት የነበሩት
መጋቤ ምሥጢር ጌራ ወርቅ ጥበቡ።

መቅድም

ዝንቱ ነገረ ኩፋሌ ፤

ይህ የኩፋሌ ታሪክ ነው ፤ ኩፋሌ ማለት ፤ ዘተከፍለ እምኦሪት ፣ ከኦሪት የተከፈለ ማለት ነው ፤ አንድም ዘይከ ፍል አውራን ወዓመታተ ወሱባኤያተ ወኢዮቤለ ፣ ወሮ ችን ዓመታቶችን ፣ ሱባኤ ዎችንና ኢዮቤሎችን የሚከ ፍል ማለት ነው ፤ ኢዮቤል ማለት አርባ ዘጠኝ ዘመን ማለት ነው ፤ ያከፋፈልን የመከፈልን ነገር የሚናገር ነገር ይህ ነው ፤ መዋዕላተ ሕግ ወስምዕ፤ ሕግ ዘጠኙ ፣ ስምዕ ኢታምልክ የተጻፈበት ዘመንን ቀንን የሚናገር ነገር ይህ ነው ፤ ዘመዋዕለ ሕግ ወስምዕ መዋዕለ ሕግ ወስ ምዕ ዝንቱ ነገረ ኩፋሌ መዋ ዕላተ ሕግ ወስምዕ ይላል ፤ አናቦ ፤ ለግብረ ዓመታት በተስብአሙ ለኢዮቤላውስቲ ሆሙ ውስተ ኵሉ ዓመታተ ዓለም ፤ በሚመላለሰው ዘመን ሁሉ በኢዮቤል ሱባዔ ውስጥ በዘመኑ ሁሉ የሚደ ረገውን ነገር የሚናገር መጽ ሐፍ ይህ ነው ፤ በከመ ተና ገሮ እግዚአብሔር ለሙሴ በደብረ ሲና አመ ዓርገ ይን ሣእ ጽላተ ዕብን ዘሕግ ወዘ ትእዛዝ በቃለ እግዚአብሔር በከመ ይቤሎ ለሙሴ ዕርግ ውስተ ርዕሰ ደብር ፤ እግዚአብሔር ሙሴን ወደ ደብረሲና ውጣ ብሎ እንደነ ገረው በእግዚአብሔር ቃል ታዝዞ በወጣ ጊዜ ፤ቱ ቃላት የተጻፉባቸው ሁለቱን ጽላት ይቀበል ዘንድ ፣ አንድም ይቀበል ዘንድ በእግዚአብሔር ቃል ታዝዞ በወጣ ጊዜ ዘመንን፣ ቀንን የሚደረገውን ነገር የሚናገር መጽሐፍ ይህ ነው ፤ ጌታ እየነገረው የጻፈውን ኦሪት ዘመተርጉ ማን ይለዋል ፤ መልአከ ገጽ ያጻፈውን ኩፋሌ ይለዋል ፤ ኦሪት ዘሳምራውያንም ይለ ዋል ፤ ዘሳምራውያትም ይላል ፤ ነገሥትን ሁለት አድርጎ የቈጠሩ እንደሆነ ሕፁፃን ከኩፋሌ ይገባል ፤ ነገሥትን አራት አድርጎ የቈ ጠሩ እንደሆነ ኩፋሌ ከሕፁ ፃን ይወጣል ፤ እስከዚህ ድረስ አርዕስት ነው ፤ ሠለ ስቱ ምዕት ለመጻሕፍት ሁሉ አርዕስት እንደሰጡ ይኸንንም አርዕስት ሰጥተዋል ፤ እሱ ግን ነገሩን ወኮነ በቀዳሚ ዓመት ብሎ ያመጣዋል ::

ምዕራፍ ፩

፩፤ ወኮነ በቀዳሚ ዓመት በጸአቶሙ ለደቂቀ እሥራኤል እምነ ግብፅ በወርኀ ሣልስ አመ አሡሩ ወሰዱሱ ለውእቱ ወርኀ፤

በሰስተኛው ወር በሰኔ በመጀመሪያ ከግብፅ በወጡ ጊዜ እንዲህ ሆነ ፤

ተናገሮ እግዚአብሔር ለሙሴ ፤

ኮነ ያለውን ተናገሮ ብሎ አመጣው ፤ በዚህ በአሥራ ስድስተኛው ወር ተነጋገረው ፤

እንዘ ይብል ዕርግ ኀቤየ ዝየ ውስተ ደብር ፤ ወእሁበከ ፪ኤ ጽላተ ዕብን ፤
ወን ፤ ታግሦ፤ ዘሕግ ዘጠኙን ፤ ወዘትእዛዝ ፤ ኢታምልክን፤ ሁለቱን ጽላት እሠጥህ ዘንድ ከዚህ ከእኔ ዘንድ ወደ ደብረሲና ውጣ ሲል ፤ አንድም ወን አግ ብቶ ሁለቱንም ጽላት እሠ ጥህለሁ ሲል ፤

ዘመጠነ ጸሐፍከ ታለብሙሙ ፤

ታስተምራቸው ዘንድ የጻፍ ክላቸውን ያህል ፤ አንድም የጻፍክላቸውን ያህል ወታለ ብሙሙ የምታስተምራቸው ንም ያህል ብሎ ለሕግ ቀጸለ ::

፪፤ ወዐርገ ሙሴ ውስተ ደብረ እግዚአብሔር ፤
ሙሴም እግዚአብሔር ወደ ሚገለጥበት ተራራ ወጣ ::
ወኀደረ ስብሐተ እግዚአብሔር ውስተ ደብረ ሲና ፤

የእግዚአብሔርም ብርሃን በደብረ ሲና ተገለጠ ፤

ወጸለሎ ደመና ለዱስ ዕለተ ለደብረ ሲና ፤

ተራራውን ብርሃን ስድስት ቀን ጋረደው የጋረደውስ ሰባት ቀን ነው በሰባተኛው ቀን ተነጋገረው ሲል ሰዱስ ዕለተ አለ ::

፫፤ ወጸውኦ እግዚአብሔር ለሙሴ በዕለት ሳብዕት በማዕከለ ደመና ፤

ሰባት ያለው ይህ ነው ፤ በደመና መካከል ሁኖ በሰባ ተኛው ቀን ሙሴን ጠራው፤
ወርእየ ስብሐተ እግዚአብሔር ከመ እሳት ዘይነድድ ውስተ ርእሰ ደብር ፤

በተራራው ራስ ላይ የእግ ዚአብሔር ብርሃን እንደ እሳት ሲነድ አየ ::

፬፤ ወሀሎ ሙሴ ውስተ ደብር አርብዓ መዐልተ ወአርብዓ ሌሊተ ፤
ሙሴም ፵ ቀን ፵ ሌሊት በተራራው ላይ ተቀመጠ ፤

ወአመሮ እግዚአብሔር ዘቀ ዳሚ፤

እግዚአብሔርም ያለፈውን አመለከተው ፤

ወዘይመጽእ ፤

የሚመጣውንም ነገረው ፤
ነገረ ኩፋሌ ኩሉ መዋዕለ ሕግ ወስምዕ ፤

ሕጉ የሚጠበቅበት አምል ኩቱ የሚነገርበት የዘመኑ ንም ሁሉ አከፋፈል ነገር አመለከተው::

፭፤ ወይቤሎ አንብር ልበከ ውስተ ኩሉ ነገር ዘአነ እነግረከ በዝንቱ ደብር ፤

በተማላ የተማላ መስማት አለና ልቦናህን አኑር አለ ፤ አንድም እንደተማላ መስ ማት አለና በዚህ ተራራ ላይ እኔ በምነግርህ ነገር ሁሉ ልቡናህን አጽና አለው ::

ወጸሐፍ ውስተ መጽሐፍ ከመ ይርአዩ ትውልዶሙ ከመ አነ ኀደግዎሙ በእንተ ኩሉ እከይ ዘገብሩ ለአስሕቶ ሥርዓት ዘአነ እሠርዕ ማዕከሌየ ወማዕከሌከ ዮም ለትውልዶሙ በደብረሲና ዘይከውን ፤

በእኔ እና በአንተ መካከል በደብረ ሲና ዛሬ በልጆቻ ቸው የሚደረገውን እኔ የምሠራውን ሥርዓት ለማ ስፈረስ ስለ ሠሩት ኃጢአት ሁሉ እንደተለየኋቸው ልጆ ቻቸው ይሰሙ ዘንድ በመ ጽሐፍ ጻፈው አለው::

፮፤ ወይዜኑ ከመዝ አመ ይመጽእ ኩሉ ዝ ነገር ላዕሌ ሆሙ ፤

ይህ ሁሉ መከራ በላያቸው በመጣባቸው ጊዜ እንደዚህ የሚደረገውን የሚናገረውን ፤ አንድም ዘይከውን ዘይዜኑ ከመዝ የሚደረገውን እንደዚህ የሚናገር በአንተና በእኔ መካከል ለልጆቻቸው እኔ ዛሬ የምሠራውን ሥርዓት ለመናቅ ለማቃለል ፤ አንድም ለማሳት ስለሠሩት ኃጢአት እንደተውኂቸው ያዩ ዘንድ ወጸሐፍ ሲል ነው በብራና ጻፈው፤ አንድም እንዳለ ይሆናል በመጽሐፍ ጻፈው አለው ፤ ከሆነ በኋላ መጽሐፍ አለ ፤

ወየአምሩ ከመ ጸደቁ አነ እምኔሆሙ በሁሉ ፍትሐሙ ወበሁሉ ምግባሮሙ ፤

በፍርዳቸው በምግባራቸው ከነሱ ይልቅ እኔ እንደረታሁ ያውቃሉ ፤

ወየአምሩ ከመ ሕልወ ኮንኩ ምስሌሆሙ ፤

ከነሱ ጋር እንደ ኖርኩ ያውቃሉ ::

፯፤ ወአንተኒ ጸሐፍ ለከ ኵሉ ዘ ቃለ ዘአነ አየድዓከ ዮም ፤ አንተም እኔ ዛሬ የነገርኩህን ይህን ሁሉ ነገር ጻፍ፤

እስመ አነ አአምር ምሪቶሙ ፤ እኔ ኃጢአታቸውን ቁጣቸውን ፤

ወክሣዶሙ ይቡስ ፤ ጽኑዐ ሲል ነው ፤

ክሣደ ልቡናቸውም ጽኑ እንደሆነ አውቃለሁና ፤

ዘእንበለ አብአሙ ውስተ ምድር እንተ መሐልኩ ለአብርሃም ወለይስሐቅ ወለያዕቆብ ፤

ለአብርሃም ለይስሐቅ ለያዕቆብ ወደማልኩላቸው አገር ወደ ኢየሩሳሌም ሳላገባቸው፤

እንዘ አብል ለዘርዕክሙ እሁብ ምድረ እንተ ታውኀዝ ሀሊበ ወመዓረ ፤

ማርና ወተትን ፤ አንድም ተድላ ደስታን የምታስገኝ አገር ኢየሩሳሌምን ለልጆቻችሁ እሰጣለሁ ብዬ ፤

ወይበልዑ ወይፀግቡ ወይትመ
የጡ ኀበ አምላክ ኪር ኀበ እለ
ኢያድኅንዎሙ እምኵሉ ምንዳቤ
ሆሙ ፤

በልተው ጠግበው ከመከራ
ቸው ሁሉ ወደማያድናቸው
ወደ ልዩ ጣዖት ይመለ
ሳሉና ::

፷፤ ወትሰማዕ ዛቲ ስምዕ
ለስምዕ ሎሙ ፤
ይህች መጽሐፍ ትመስክር
ባቸው ፤
እስመ ይረስዑ ትእዛዘየ ዘኵሉ
አነ እኤዝዞሙ ፤
እኔ የማዛቸውን ትእዛዝ
ሁሉ ረስተዋልና ፤
ወየሐውሩ ድኅረ አሕዛብ ወድ
ኅረ ርኵሶሙ ወድኅረ ኀጣ
ሮሙ፤
ሁሉንም ጠቅሎ ጣዖትን
ያመልካሉና ፤
ወይትቀነዩ ለአማልክቲሆሙ ፤
ለጣዖቶቻቸው ይገዛሉ ::
ወይከውንዎሙ ማዕቀፈ ለምን
ዳቤ ወለዓዕር ወለመሥገርት ፤
መከራን ጭንቅን ጦርን
ለማምጣት ለዚህ ሁሉ
መሰናክል ይሆኑባቸዋል ::

፷፩፤ ወይትኀሥሉ ብዙኃን
ወይትአኃዙ ፤
ብዙ ሰዎች በመከራ ይያ
ዛሉ ይጠፋሉ ፤
ወይወድቁ ውስተ እደ ፀር ፤
በጠላቶቻቸውም እጅ ይወ
ድቃሉ ፤
እስመ ኃደጉ ሥርዓትየ ወትእ
ዛዝየ ፤
አዝዤ የሠራሁትን ሕግ ፤
ወበዓላተ ኪዳንየ ፤
ምዬ የሠራሁትን በዓለ
ፋሲካን ፤ በዓለ መጸለትን፤
በዓለ ሰዊትን ::
ወሰንበታትየ ፤
ቅዳሜ ቅዳሜን
ወቅድሳትየ ዘቀደስኩ ሊተ
በማዕከሌሙ ፤
በመካከላቸው እኔ የለየሁ
ትን ንዋየ ቅድሳትን ፤
ወደብተራየ፤
ኻያውን ክንድ፤
ወመቅደስየ ዘቀደስኩ ሊተ በማ
ዕከለ ምድር ፤
በምድር መካከል ለኔ የለየ
ሁትን አሥሩን ክንድ ፤
አንድም ደብተራየ ፤ ደብ
ተራ አሪትን ፤

መቅደስየ ፤ ቤተ መቅደስን
ዘንግተዋል ረስተዋልና ይጠ
ፋሉ ፤

ከመ እሚም ስምየ ላዕሌሁ ወከመ ይጎድር ፤
ስሜን በሱ አስጠራ ዘንድ ፤ ስም አጠራሬ ጸንቶ ይኖር ዘንድ ፤ ላዕሌሁ ፤ ለመቅደስ ፤ ለደብተራም ነው ::

፲፤ ወይገብሩ ሎሙ ፍሥሐ ታተ ፤
ተራራ ያበጃሉ ፤ አንድም ተራራውን ያመልካሉ ፤
ወያመ ፤
መስጊድ ያበጃሉ ::
ወግልፎ ፤
ጣያት ይቀርፃሉ እንዲህ አድርገው ፤
ወይሰግዱ ዘዘሊአሆሙ ፤
እየገንዘባቸው ይሰግዳሉ ፤
ለስሒት ፤
ከሕገ እግዚአብሔር ወጥቶ ለመሳት ጣኦት ለማምለክ ፤
ወይዘብሑ ውሉዶሙ ለአጋንንት ወለኵሉ ግብረ ስሕተተ ልቦሙ ፤
ልቡናቸውን ለሚያስት ሥራ ሁሉ ልጆቻቸውን ይሠዋሉ ፤
ወእፈኑ ኀቤሆሙ ሰማዕተ ከመ አስምዕ ሎሙ ወኢይሰምዑ ፤
አለማባቸው አዳኝባቸው ዘንድ የሚመክሩ የሚያስተምሩ ነቢያት ካህናትን ወደነሳቸው እልካለሁ አይሰሙም ፤
ወለማዕተኒ ይቀትሉ ፤
ነቢያት ካህናትን ይገድላሉ::

፲፩፤ ወለእለኒ የኀሥሡ ሕገ ይቀትልዎሙ ወይሰድድዎሙ ፤
ሕግን የሚሹ ሕግን የሚጠብቁትንም ሰዎች ይገድሏቸዋል ያሳድዱዋቸዋል ፤
ወኵሉ ያጸርዑ ፤
ሁሉን ያቦዝናሉ ፤ አንድም ኃጢአትን ያሠራሉ ጣያትን ያስመልካሉ ፤
ወይዌጥኑ ለገቢረ እኩይ በቅድመ አዕይንትየ ፤
በፊቴም ኃጢአት መሥራትን ይጀምራሉ ጣያትን ያመልካሉ ::

፲፪፤ ወአኀብዕ ገጽየ እምኔሆሙ ፤
ከነሱ ገጸ ረድኤቴን እሠውራለሁ ማለት ፊት እነሣቸዋለሁ ፤
ወእሜጥዎሙ ውስተ እደ አሕዛብ ለዔዋዊ ወለሕብልያ ወለተበልዖ ፤

ለምርኮ፤ ለብዝበዛ ፤ ለመበ
ላት፤ ለዘረፋ፤ ይሆኑ ዘንድ
ለአሕዛብ አሳልፌ እሠጣቸ
ዋለሁ እጥላቸዋለሁ ፤
ወአሴስሎሙ እማዕከለ ምድር ፤
ከኢየሩሳሌምም መካከል አጠ
ፋቸዋለሁ ፤
፲፫፤ ወአዘርዎሙ ማዕከለ አሕ
ዛብ ፤
በአሕዛብ መካከል እበትናቸ
ዋለሁ ፤
ወይረሥኡ ኵሎ ሕግየ ፤
ሕጌን ሁሉ ማለት ዘጠኑን
ሕግጋት ፤
ወኵሉ ትእዛዝየ ፤
ትእዛዜንና ኢታምልክን ፤
ወኵሉ ፍትሕየ ፤
ፍርዴን ሥርዓቴንም ሁሉ
ይዘነጋሉ ፤
ወይስሕቱ ሠርቀ ወሰንበተ ፤
ቅዳሜንና ሠርቀ ወርኀን ፤
ወበዓለ ፤
በዓለ ፋሲካን፤ በዓለ
መጸለትን፤ በዓለ ሰዊትን ፤
ወኢዮቤለ ፤
፵፬ኙን ዘመን ፤
ወሥርዓተ ፤
ሥርዓትንም ዘንግተዋል
ረስተዋልና ::
፲፬፤ ወእምዝ ይትመየጡ ኀቤየ
እማዕከለ አሕዛብ በኵሉ ልቦሙ
ወበኵሉ ነፍሶሙ ወበኵሉ
ኃይሎሙ ፤
ከዚህ በኋላ በፍጹም ሰው
ነታቸው በፍጹም ልቡና
ቸው በፍጹም ዕውቀታቸው
በአሕዛብ መካከል ከአምል
ኮተ ጣዖት ወደኔ ይመ
ለሳሉ ፤
ወአስተጋብኦሙ እማዕከለ አሕ
ዛብ ፤
እኔም ከአሕዛብ ሁሉ መካ
ከል እሰበስባቸዋለሁ::
፲፭፤ ወየኀሥሡኒ ከመ እት
ራከቦሙ ፤
እገለጽላቸው ዘንድ ይፈልጉ
ኛል ፤ አንድም በሰባ ዘመን
ይሹኛል በረድኤት እገናኛ
ቸው ዘንድ ፤ አንድም በ፸
ሺሕ ካሬ መቶ ዘመን ይሹ
ኛል ሰው ሁኜ ሥጋ ለብሼ
እገለጽላቸው ዘንድ ፤
ወሶበ የሐሥሡኒ በኵሉ ልቦሙ
ወበኵሉ ነፍሶሙ አነ እከሥት
ሎሙ ብዙኃ ሰላመ በጽድቅ ፤
በፍጹም ሰውነታቸውና በፍ
ጹም ልቡናቸው በፈለጉኝም
ጊዜ እኔ በእውነት ብዙ
ፍቅርን አንድነትን እገልጥ
ላቸዋለሁ ፤

ወአፈልሶሙ ተክለ ርትዕ በሎሱ ልብየ ወበሎሱ ነፍስየ ፤
ሕግ እንዲጠብቁ አድርጌ በፍጹም ልቡና ወደ ቀና ሕግ እመልሳቸዋለሁ፤ አን ድም ከባቢሎን ከገሀነም አወጣቸዋለሁ ::

፲፮፤ ወይከውኑ ለበረከት ወአኮ ለመርገም ፤
ለመርገም ያይደለ ለበረከት ይሆናሉ ፤
ወይከውኑ ርእሰ ወአኮ ዘነበ ፤
ተገዥ ያይደሉ ገዥ ይሆ ናሉ ፤
ወአሐንፅ መቅደስየ ማዕከ ሎሙ፤
በመካከላቸው ደብተራ አሪ ትን እሠራለሁ ፤ አንድም ቤተ መቅደስን አንፃለሁ ፤ አንድም ማህፀነ ማርያምን አንፃለሁ ፤ አንድም መስቀ ልን እሠራለሁ፤ አንድም ቤተ ክርስቲያንን እሠራ ለሁ፤
ወአኃድር ምስሌሆሙ ፤
ከእነሱ ጋራ በረድኤት እኖ ራለሁ ፤
ወእከውኖሙ አምላኮሙ ፤
የፍቅር አባት እሆናቸዋ ለሁ፤
ወእሙንቱኒ ይከውኑኒ ሕዝብየ ዘበአማን ወዘበጽድቅ ፤
እነሳቸውም በሚገባ በእው ነት ልጀቼ ይሆኑኛል ፤
ወኢየኃድጎሙ እንከ ወኢይትና ከሮሙ እስመ አነ እግዚአብሔር አምላኮሙ ፤
ፈጣሪአቸው እኔ እግዚአብ ሔር ነኝና ፈጽሜ አልለያ ቸውም አለው ::

፲፯፤ ወወድቀ ሙሴ በገጹ ወጸለየ ፤
ሙሴም በግንባሩ ተደፍቶ ለመነ ፤
ወይቤ እግዚኦ አምላኪየ ኢትኅ ድግ ሕዝበከ ወርስተከ እስራኤለ ለሐዊር በስሕተተ ልቦሙ ፤
አቤቱ ፈጣሪየ በልቡናቸው ስሕተት ጸንተው ለመኖር ወገኖችህን ማደሪያዎችህን እስራኤልን አትተው ፤
ወኢትመጥዎሙ ውስተ እደ ፀሮሙ አሕዛብ ከመ ይኵንን ዎሙ ወከመ ይግበርዎሙ ይኅጥኡ ለከ ፤
የአብሱ ኪያከ ሲል ነው ፤
አንተን ይበድሉ ዘንድ እንዲበድሉ

እንዳያደርጓቸው በጠላቶቻቸው በአሕዛብ እጅ አሳልፈህ አትስጣቸው ::

፲፰፤ ወይትለዓል እግዚኦ ምሕረትከ ላዕለ ሕዝብከ ፤ አቤቱ ይቅርታህ ፤ ቸርነትህ በወገኖችህ ላይ ይገለጥ ፤

ወፍጥር ሎሙ መንፈሰ ርቱዐ፤ ቅን ልቡና ትሑት ሰብእና አሳድርባቸው ፤ አንድም ዕውቀትን አሳድርባቸው ፤

ወኢይኰንኖሙ መንፈሰ ቤል ሆር ለአስተዋድዮቶሙ ቅድሜከ ወለአዕቅፆቶሙ እምኵሉ ፍናተ ጽድቅ ከመ ይትጋጐሉ እምቅድመ ገጽከ ፤

በፊትህ ከባለሟልነትህ ወጥተው ይጠፉ ዘንድ ለማጣላት ከእውነተኛውም ሕግ ሁሉ ለማስነካከል የዲያብሎስ ፤ አንድም የሰይጣን ሥልጣን አይግዛቸው፤ ቤል ሆር ማለት መስተዋድይ ፤ ዘአልቦ አርዑት ማለት ሥልጣን የሌለው ማለት ነው ::

፲፱፤ ወእሙንቱሰ ሕዝብከ ወርስትከ ዘባሕኮሙ በኃይልከ ዓቢይ እምእደ ግብፅ ፤ እነሳቸውም በጽኑ ሥልጣንህ በገናና ኃይልህ ከግብፅ ሰዎች እጅ ያዳንካቸው ወገኖችህ ማደሪያዎችህ ናቸው፤ አንድም ናቸውና፤ ፍጥር ሎሙ ልበ ንጹሐ ወመንፈሰ ቅዱሰ ፤ ንጹሕ ልቡናን ፍጠርላቸው ማለት ከቂም ከበቀል ከተንኮል ክፉ ከማሰብ በልብ ከመያዝ ንጹሕ አድርጋቸው ጽኑ ዕውቀትንም አሳደርባቸው ሲል ነው ፤

ወኢይትዓቀጹ በኃጢአቶሙ እምይእዜ ወእስከ ለዓለም ፤ ከዛሬ ጀምሮ እስከ ዘለዓለም ድረስ በኃጢአት አይሰነካከሉ አለ ::

፳፤ ወይቤሎ እግዚአብሔር ለሙሴ አነ አአምር ፤ እግዚአብሔርም ሙሴን እንዲህ አለው ፤

ተዋሥኦቶሙ ፤ እኔ ክርክራቸውን ፤

ወሕሊናሆሙ ፤ አሳባቸውን ፤

ወይቡሰ ክሣዶሙ ፤

ክሣደ ልቡናቸው ጽኑ እን ሆነ አውቃለሁ ፤
ወኢይሰምዑ እስከ ሰባ የአምሩ ኃጢአቶሙ ወኃጣውአ አበዊ ሆሙ ፤
የአባቶቻቸውን ኃጢአት ፤ ፍዳና የራሳቸውን ኃጢአት ፍዳ እስኪያውቁ ድረስ አይ ሰሙም ::

፳፩፤ ወእምድኅረ ዝንቱ ይትመየጡ ኀቤየ በኵሉ ርትዕ ወበኵሉ ልብ ወበኵሉ ነፍስ ፤
ከዚህ በኋላ በፍጹም ቅን ነት በፍጹም ልቦና በፍጹም ሰውነት በሚገባ ወደ እኔ ይመለሳሉ ፤
ወአወቂ ሞልፈተ ልቦሙ ወቊ ልፈተ ልበ ዘርኦሙ ፤
እገዝር ሲል ነው ፤ የልጆ ቻቸውን ልቡና ቈላፍነትና የልቡናቸውን ቈላፍነት እቈ ርጣለሁ አለ ድንቊርናቸ ውን አርቃለሁ ሲል ነው::

፳፪፤ ወእፈጥር ሎሙ መንፈሰ ቅዱሰ ወአነጽሖሙ ከመ ኢይ ትመየጡ እምድኅሬየ እምይእቲ ዕለት እስከ ለዓለም ፤
ቅን ንጹሕ ልቡናን እፈጥር ላቸዋለሁ ከዚያች ቀን ጀምሮ ለዘለዓለም ወደ ጣዖት ወደኃጢአት እንዳይ መለሱ እንዲህ አድርጌ አርቄ ዕውቀትን አሳድርባ ቸዋለሁ አነሣቸዋለሁ ፤
ወትተሉ ነፍሶሙ ኀቤየ ፤
ሰውነታቸውም እኔን ትከተ ላለች ታመልከኛለች ፤
ወኵሉ ትእዛዘየ ፤
ሕጌንም ትእዛዜንም ሁሉ ይፈጽማሉ ::

፳፫፤ ወአከውኖሙ አበ ፤
የፍቅር አባት እሆናቸዋ ለሁ ፤
ወእሙንቱኒ ይከውኑኒ ውሉ ድየ ፤
እነሳቸውም የፍቅር ልጆቼ ይሆኑኛል ፤
ወይሰመዩ ኵሎሙ ውሉደ አምላክ ሕያው ፤
ሁሉም በሕያውነት የሚ ኖር የእግዚአብሔር ልጆች ይባላሉ ፤
ወየአምሮሙ ኵሉ መልአክ ፤
ንጉሥ ሁሉ ፤
ወኵሉ መንፈስ ፤
ሰውም ሁሉ ያውቃቸዋል ፤
ወየአምርዎሙ ከመ እሙንቱ ውሉድየ ፤

እነሳቸው የፍቅር ልጆቼ እንደሆኑ ያውቋቸዋል ፤
ወአነ አቡሆሙ በጽድቅ ወበ ርትዕ ፤
እኔም በሚገባ በእውነት የፍቅር አባታቸው እንደሆ ንኩ
ወአፈቅሮሙ ፤
እንድወዳቸውም ያውቁኛል ፤

፳፬፤ ወአንተ ጸሐፍ ለክ ኵሎ ዘንተ ነገረ ዘአነ አየድዐክ በዝንቱ ደብር ዘቀዳሚ ወዘደኃሪ ወዘይ መጽእ ወዘሀሉ በኵሉ ኩፋሌ መዋዕል ዘበሕግ ወዘበስምዕ ፤ ወዘበሱባዔሆሙ ለኢዮቤሌዎን እስከ ለዓለም ፤ ወእስከ ሶበ እወርድ እምሰማይ ዲበ ምድር ወአኃድር ምስሌሆሙ በኵሉ ለዓለመ ዓለም ፤
ለዘለዓለም ከሰማይ እስክ ወርድ ለዘለዓለም በሁሉ በነሱ በረድኤት እስካድር ድረስ በኢዮቤል ሱባዔ ውስጥ ዘጠኙ ሕግ ኢታ ምልክ በተጻፈበት በዘመኑ አክፋፈል በኩፋሌ ሁሉ ያለ ውን የሚመጣውን የፊ ቱን የኋላውንም በዚህ ተራራ ላይ የነገርኹህን ይህን ነገር ሁሉ ጻፍ አለው ::

፳፭፤ ወይቤሎ እግዚአብሔር ለመልአከ ገጽ ጸሐፍ ለሙሴ ፤
ባለሚልነት ያለው መል አኩን ለሙሴ ጻፍለት አለው ፤
እምቀዳሚ ፍጥረት እስከ አመ ይትሐነፅ መቅደስየ በማዕከ ሎሙ ለዓለመ ለዓለም ፤
ዓለም ከተፈጠረ ከመጀመ ሪያው ፍጥረት ጀምሮ ደብተራ ኦሪት እስኪሠራ ድረስ ፤ አንድም ቤተ መቅደስ እስኪታነፅ ድረስ፤ አንድም ማኅፀነ ማርያም እስኪዘጋጅ ድረስ ፤ አን ድም መስቀል እስኪተከል ድረስ ፤ አንድም ቤተ ክር ስቲያን እስኪሠራ ድረስ ፤
ወያስተርኢ እግዚአብሔር ለዓ ይነ ኵሉ ፤
እግዚአብሔርም ለሰው ሁሉ እስኪገለጥ ድረስ ለሙሴ ጻፍለት አለው ::

፳፮፤ ወየአምር ኵሉ ከመ አነ አምላክ እሥራኤል ወአብ ለኵሎሙ ደቂቀ ያዕቆብ ፤

የእሥራኤል ፈጣሪ ለያዕቆብ ልጆች ሁሉ የፍቅር አባት እኔ እንደሆንኩ ሁሉ እስኪያውቅ ድረስ ፤
ወንጕሥ በደብረ ጽዮን ለዓለመ ዓለም ፤
በደብረ ጽዮንም ፤ ለዘለዓለም ገሸ እንደሆንኩ ፤ በደብተራ ኦሪት፤ አንድም በቤተ መቅደስ ፤ አንድም በማኅፀነማርያም ፤ አንድም በመስቀል ፤ አንድም በቤተ ክርስቲያን ፤ አንድም በምጽአት በደብረ ጽዮን ንጉሥ እንደሆንኩ ሁሉ እስኪያውቁ ድረስ ጸፍ አለው ፤
ወትከውን ጽዮን ኢየሩሳሌም ቅድስተ ፤
ጽዮን የምትባል ኢየሩሳሌ ምም ቅድስት ክብርት ትሆናለች ፤

ምዕራፍ ፪

፩፤ ወነሥአ መልአከ ገጽ ዘየሐውር ቅድመ ተዓይኒሆሙ ለእሥራኤል ጽላተ ዘኩፋሌ ዓመታት ፤
ከእስራኤል ሠራዊት ፊት የሚሔድ መልአከ ገጽም የዘመኖች አከፋፈል የተጻፈበትን ጽላት ያዘ ::
፪፤ እምአመ ፍጥረተ ዓለም ለሕግ ወለስምዕ በሱባዔሆሙ ለኢዮቤልዮን በበዓመት እምዕለተ ፍጥረት ሐዳስ እስከ አመ ይትሔደሳ ሰማያት ወምድር ወኵሉ ፍጥረቶሙ ፤
ሕግ ዘጠኙ ፣ ስምዕ ኢታ ምልክን ፣ ለመጠበቅ አዳም ከተፈጠረ ጀምሮ አዲስ ዘመን ከተፈጠረበት ቀን ጀምሮ ለሰማያት ዝናም በማዝነም እስኪታደሱ ድረስ ምድርም የዘሩባትን በማብቀል የተከሉባትን በማጽደቅ እስክትታደስ ድረስ ፤
ወኵሉ ፍጥረቶሙ ፤
ግብረቶሙ ሲል ነው ግብራቸው እስኪታወቅ ድረስ ፤
በከመ ጎይላቲሆሙ ለሰማይ ፤
ለሰማያት ሲል ነው፤ የሰማያትም ሠራዊት ፤ ፀሐይ፤ ጨረቃ ፤ ከዋክብት እንደ መሆናቸው ::
፫፤ ወበከመ ኵሉ ፍጥረተ ምድር ፤
የምድር ሠራዊት እንደ መሆናቸው እንስሳት አራዊት ሁሉ እስኪታደሱ ድረስ ፤

እስከ አመ ይትፈጠር መቅደስ እግዚአብሔር በኢየሩሳሌም ወበደብረ ጽዮን ፤
በኢየሩሳሌም ደብተራ አሪት እስክትሠራ ፤ አንድም ቤተ መቅደስ እስክትታነጽ፤ ማኅፀነ ማርያም እስኪዘጋጅ ፤ አንድም መስቀል እስኪተከል ድረስ ፤ አንድም ቤተ ክርስቲያን እስኪሠራ ድረስ ዓለምን ዘመንን የሚከፍል፤ ዘመን የሚቆጠርበት ሕግን የሚጠብቅ የሙሴን ልብ ያዘ ፤ ጽላት ያለው ልብን ነው ፤ ይህ በዔዋዊ ጊዜ ነው ፤ አንድም ሰማይ ፤ ልዑላኑ በመከራ እስኪታደሱ ፤ ድረስ ፤ ወምድር ፤ ትሑታኑም በመከራ እስኪታደሱ ድረስ ግብራቸውም እስኪታደስ ድረስ ፤ አንድም ፀሐይ ጨረቃ ከዋክብት ባለመመለክ እስኪታደሱ ድረስ ግብራቸው የሰማይ ሠራዊት የምድርም ሠራዊት እንደመሆናቸው ፤ አንድምፀሐይ ንጉሡ፤ ጨረቃ ሊቀ ካህናቱ ፤ ከዋክብት ሠራዊቱ በዔዋዊ ጊዜ በመማረክ እስኪታደሱ ድረስ ግብራቸው እስኪታደስ ድረስ ፤ አንድም በኢየሩሳሌም ደብተራ አሪት እስክትተከል ድረስ ፤ አንድም ቤተ መቅደስ እስክትሠራ ድረስ ፤ አንድም ማኅፀነ ማርያም እስኪዘጋጅ ድረስ ፤ አንድም መስቀል እስኪተከል ድረስ፤አንድም ቤተ ክርስቲያን እስኪሠራ ድረስ ፤ ነሥአ ጽላተ የሙሴን ልብ ያዘ፤ ይህም በዔዋዊ ነው ፤ አንድም ፀሐይ ጨረቃ ባለመመለክ ፤ ከዋክብት ባለመመለክ እስኪታደሱ ድረስ፤ አንድም ፀሐይ ንጉሡ ፤ ጨረቃ ሊቀ ካህናቱ ፤ ከዋክብት ሠራዊቱ በሚጠት እስኪታደሱ ድረስ ፤ ዕፀው አዕባን ባለመመለክ እስኪታደሱ ድረስ ፤ አንድም ሕዝቡ እስራኤል በሚጠት እስኪታደሱ ድረስ፤ አንድም ፀሐይ የባቢሎን ንጉሡ ፤ ጨረቃ ቤት ወደዱ ፤

ከዋክብት ሠራዊቱ ዕፀው አዕባን ሕዝቡ አሕዛቡ በሚ
ጠት ጊዜ ባለመማረክ እስ
ኪታደሱ ድረስ ፤ ግብራ
ቸውም የሰማይ የምድር
ሠራዊት እንደመሆኑ ፤
ነሥአ ጽላተ ነው ፤ ይህ
በሚጠት ነው ፤ አንድም
ሰማይ በማዝነም ምድርም
በማብቀል በማጽደቅ እስኪ
ታደሱ ድረስ ፤ ነሥአ
ጽላተ የሙሴን ልቡና ያዘ፣
ይህም በሚጠት ነው ፤
አንድም ልዑላኑ ትሑታኑ
በሕግ እስኪታደሱ ድረስ
ግብራቸውም እንደ ፀሐይ
እንደ ጨረቃ እንደ ከዋክ
ብት ፤ እንደ ዕፀው እንደ
አዕባን ፤ ባለመመለክ እስኪ
ታደሱ ድረስ ፤ እሊህም
በሕግ እስኪታደሱ ድረስ ፤
አንድም በሥጋዌ ጊዜ
መለኮት ትስብእት በተዋ
ህዶ፣ በዕለተ ልደትም ጊዜ
መላእክት ኖሎት በምስ
ጋና እስኪታደሱ ድረስ ፤
ግብራቸውም የሰማይ የም
ድር ሠራዊት እንደመሆኑ
እስኪታደስ ድረስ፣ አንድም
ነፍሳት ሥጋት በትንሣኤ
ዘጉባዔ በሐዲስ ተፈጥሮ
እስኪታደሱ ድረስ ፤ ግብ
ራቸውም የሰማይ የምድር
እንደመሆኑ እስኪታደስ
ድረስ፣ ነሥአ ጽላተ ፤ ይህ
በሥጋዌ በምጽአትም ነው፣
አንድም መንግሥተ ሰማ
ይን ገሃነምን በመውረስ
እስኪታደሱ ፤ ድረስ ግብራ
ቸውም የሰማይ የምድር
እንደመሆኑ እስኪታደሱ
ድረስ ፤ ነሥአ ጽላተ የሙ
ሴን ልቡና ያዘ ፤ አንድም
መንግሥተ ሰማይ ገሃነም
በመወረስ እስኪታደሱ
ድረስ ግብራቸውም በጎል
ፈት ጊዜ ባለማለፍ ጸንቶ
ለመኖር እስኪታደሱ ድረስ ፤
ነሥአ ጽላተ ብለህ እሠር፣
መወረሳቸውን ተሐድሶ ፤
አለመወረሳቸውን ብሌት
አድርጎ የተናገረው ይህ
ነው ፤

ወኵሉ ብርሃናት ይትሔደሱ ለፈውስ ወለሰላም ወለበረከት ለኵሎሙ ጎሩያነ እስራኤል ፤ ከእስራኤል ለተመረጡ ሁሉ ፤ ለድኅነት ለፍቅር፣ ለአንድነት ለበረከት ሊሆኑ ብርሃናት እስ ኪታደሱ ድረስ ፤

ወከመ ይኩን ከማሁ እምይእቲ ዕለት ወእስከ ዙሉ መዋዕለ ምድር ፤
ከዚች ቀን ጀምሮ ዘመን እስከሚመላለስበት ቀን ድረስ አሁን እንደ ተናገርኩት ይሆን ዘንድ ይደረግ ዘንድ ::

፬፤ ወይቤሎ መልአከ ገጽ ለሙሴ በቃለ እግዚአብሔር እንዘ ይብል ጸሐፍ ኩሎ ነገረ ፍጥረት ፤
ባለሚልነት ያለው መልአክም ሙሴን በሕገ እግዚአብሔር ቃል ታዝዞ የፍጥረትን ነገር ሁሉ ጻፍ ብሎ ነገረው ፤
ከመ በሰዱስ ዕለት ፈጸመ እግዚአብሔር አምላክ ኩሎ ግብሮ ወኩሎ ዘፈጠረ ፤
ፈጣሪ እግዚአብሔር በስድስተኛው ቀን ፍጥረቱን ሁሉ ፈጥሮ እንደ ጨረሰ ጻፍ አለው ::

፭፤ ወአሰንበተ በሳብዕት ዕለት፤
በሰባተኛው ቀን በዕለተ ቀዳሚት ዕረፍት እንዳደረገ ፤
ወቀደሳ ለኩሉ ዓለማት ፤
ቀዳሚትን ለዓለም ሁሉ እንደለያት ፤ ከዕለታት እንደለያት ሲል ነው ፤
ወአክበራ፤
እንዳከበራት ፤
ወአንበራ ትእምርተ ለኩሉ ግብሩ ፤
ለሥራው ሁሉ ምልክት እንዳደረጋት የፍጥረትን ነገር ሁሉ ጻፍ አለው ፤
እስመ በዕለት ቀዳሚት ፈጠረ ሰማያተ እለ መልዕልት ፤
በመጀመሪያቱ ቀን በዕለተ እሁድ በላይ ያሉ ሰማዮችን ፈጥሯልና ፤
ወምድረ ወማያተ ወኩሎ መንፈሰ ዘይትለዓክ ቅድሜሁ ፤
ምድርንም ውሃዎችንም በፊቱ የሚያገለግል ፍጥረትንም ሁሉ ፈጥሯልና ፤

፮፤ ወመላእክተ ገጽኒ ፤
ባለሚልነት ያላቸው መላእክትን ፤ ወመላእክተ ቅዳሴ የሚያመሰግኑ መላእክትን፤
ወመላእክተ መንፈሰ እሳት ፤
በእሳት አካል ላይ የተሾሙ መላእክትን ፤
ወመላእክተ መንፈሰ እስትን ፋስ፤

በነፋሳት አካል ላይ የተ
ሾመ መላእክትን ፤
ወመላእክተ መንፈሰ ደመናት ፣
አካለ ደመናት ሲል ነው ፤
በደመናት አካል ላይ
የተሾመ መላእክትን ፤
ወለጽልመት ወለኵሉ በረድ
ወለአስሐትያ ፤
በጨለማና በብርሃን አካል
ላይ በውርጭና በበረድ
ሁሉ ላይ የተሾመ መላእ
ክትን ፈጥሯልና ::

፯፤ ወመላእክተ ቀላያት ፤
በውሀ ላይ ፤
ወነጐድጓዳት ወለመባርቅት ፤
በመብረቅና በነጐድጓዳት ላይ፣
ወመላእክተ መናፍስት ፣
ተሐውሶ ያላቸው ሲል ነው
በነፋሳት ላይ የተሾመ
መላእክትን ፤
ለቊር ወለመርቁ ፣
በቀቅና በውርጭ ፣
ወክረምት ወለመፀው ፤
በክረምትና በመፀው ፤
ወለማዕረር ወለሐጋይ ፣
በበጋና በፀደይ ፣
ወለኵሉ መናፍስተ ተግባሩ
ዘበሰማያት ወዘበምድር ፣
ሠራዊተ መላእክት ሲል
ነው ፣ በምድርና በሰማይ
ባሉ ነፋሳት ሁሉ ላይ ፣
ወዘበኵሉ ቀላያት ፣
በወንዙ ሁሉ ላይ ፣
ወጽልመት ወብርሃን ፣
በብርሃንና በጨለማ ሁሉ
ላይ ፣
ወነህ ወምሴት ፣ በምሽትና
በመንጋት ላይ ፣
ዘአስተዳለወ በአእምሮ ልቡ ፣
እሊህን የሚመግቡ መላእክ
ትን እግዚአብሔር በባሕ
ርይ ዕውቀቱ ፈጥሯልና
ጸሐፍ ብለህ እሠር ::

፰፤ ወአሜሃ ርኢነ ምግባሮ
ወባረክናሁ ፣
ያን ጊዜ ሥራውን ፍጥረ
ቱን አይተን አመሰገነው፣
ወሰባሕነ ቅድሜሁ በእንተ ኵሉ
ምግባሩ ፣

ኪያሁ ሲል ነው ፤ ስለፍ
ጥረቱ ሁሉ እሱን አመሰ
ገነው ፤
እስመ ፭ተ ግብረ ዓቢያተ ገብረ
በቀዳሚት ዕለት ፤
በመጀመሪያቱ ቀን በዕለተ
እሁድ ሰባት ታላላቆች
ፍጥረቶችን ፈጥሯልና ::

፱፤ ወበሳኒታ ዕለት ገብረ ምጽንዓተ ማዕከለ ማይ ፤
በሁለተኛውም ቀን ሰኞ በሐኖስና በውቅያኖስ መካ
ከል ጠፈርን ፈጥሯልና ፤
ተከፍሉ ማያት በይእቲ ዕለት ፤
በዚያችም ቀን ውሀዎች ተከፍለው ፤
መንፈቆሙ ዐርጉ ላዕለ ፤
እኩሌቶቹ ወደ ላይ ወጡ ፤
ወመንፈቆሙ ወረዱ መትሕተ ምጽንዓት ማዕከለ ዲበ ገጻ ለዙላ ምድር ፤
እኩሌቶቹ ከጠፈር በታች ወዳሉ ወደ ምድር መካከል ወደ ውቅያኖስ ወረዱ ፤
ጠፈር ከምድር በላይ ከመ ካከል ቀረ ፤
ወዘንተ ባሕቲቶ ግብረ ገብረ በሳኒታ ዕለት ፤
በሁለተኛው ቀን ሰኞ ይህን ፍጥረት ብቻ ፈጠረ ::

፲፤ ወበሣልስት ዕለት ገብረ በከመ ይቤ ማያት ይኅልፉ እም ቅድመ ገጻ ለዙላ ምድር ውስተ ፩ዱ መካን ወያስተርኢ የብስ ፤
በሦስተኛዪቱም ቀን ማክ ሰኞ ውሀዎች ከምድር ላይ ወደ አንድ ቦታ ሄደው ይወሠኑ ምድርም ትገ ለጥብሎ እንደ ተናገረው አደረገ ::

፲፩፤ ወገብሩ ከማሁ ማያት በከመ ይቤሎሙ ፤
ውሀዎችም እንዳአዘዛቸው እንደዚሁ ተዘጋጁ ፤
ወተግኀሡ እምዲበ ገጻ ለምድር ውስተ መካን ፩ አፍኣ በምጽ ንዓት ዝየ ፤
ከዚህ ከምድር ላይ በአፍኣ ወደሆነ ወደውቅያኖስ ተወ ገዱ ፤ አንድም ከጠፈር አፍኣ ወደሆነ ወደዚህ ወደ ውቅያኖስ ተወሰኑ ፤
ወአስተርአየት የብስ ፤
ምድርም ተገለጠች ::

፲፪፤ ወበይእቲ ዕለት ፈጠረ ላቲ ልዮታተ ዘአብሕርት በበም ጕባዓቲሆሙ ፤

በዚያችም ቀን በየመሰብሰ ቢያቸው በውቅያኖስ የባ ሕር ጥልቆችን ፈጠረ ሠራ ላት ፤

ወኵሎሙ አፍላግ ወምጉባዓ ቲሆሙ ለማያት ውስተ አድባር ወውስተ ኵላ ምድር ወኵሎሙ ምዕቃላት ወኵሎ ጠለ ምድር ፤

ፈሳሾችንም ሁሉ የውሀም ችንም መወሠኛዎች በተ ራራ ሥር በምድር ውስጥ ሁሉና በተራራዎች ሥር ያሉ የውሀዎችንም መወሠ ኛዎች ምንጮችም ሁሉ በምድር ያሉ የውሀዎችንም ጕድጓድ ሁሉ ፈጠረላት ፤

ወዘርዐ ዘይዘራዕ በበዘርዑ ወኵሎ ዘይትበላዕ ወዕፀወ እሊ ይፈርዩ ወያማተ ፤

በየዘሩ የሚዘራውን ዘር የሚበላውንም ዘር ፤

ወገነተ ኤዶም ለተድላ ወኵሎ ፬ተ ዘንተ ዐበይተ ትውልደ ገብረ በዕለት ሣልሲት ፤

የሚያፈሩ እንጨቶችንም ዛፎችንም በገነት ለተድላ ደስታ የተፈጠሩ ተክሎችን በሦስተኛዪቱ ቀን በዕለተ ሠሉስ አራት ፍጥረትን ፈጠረ ፤ መናፍቃን ሶስት ፍጥረት ፈጠረ ይላሉና ፤

ኩፋሌ ወኵሎ ፬ተ ዘንተ ዓበይተ ትውልደ በዕለት ሣልሲት ብሎ ፬ትፍጥረትን ፈጠረ ብሎ ያፈርስባችዋል ያለው ይህንን ነው ::

፲፫ ፤ ወበራብዕት ዕለት ገብረ ፀሐየ ወወርኀ ወከዋክብተ ወአንበሮሙ ውስተ ምጽንዓተ ሰማይ ይቁሙ ወከማሁ ያብርሁ ውስተ ኵሉ ምድር ፤

በአራተኛዪቱም ቀን ጨረቃ ንና ፀሐይን ከዋክብትን ፈጥሮ በዓለሙ ሁሉ ያበሩ ዘንድ በጠፈር አኖራቸው ፤

ወአኰኑኖሙ መዓልተ ወሌሊተ፤ ሌሊትንና ቀንንም አስገዛ ቸው ፤

ወለፈሊጥ ማዕከለ ብርሃን ወጽ ልመት ፤

በጨለማና በብርሃን መካ ከል ለመለየት ድምበር አደ ረጋቸው ፤

፲፬ ፤ ወወሀበ እግዚአብሔር ፀሐየ ለትእምርት ዐቢይ ዲበ ምድር ወለመዋዕል ወለሰን በታት፤

እግዚአብሔርም በምድር ላይ ደግ ምልክት ሊሆን ለሱባኤዎችና ለቀኖች ፤

ወለአውራኅ ወለበዐላት ፤
ለበዓላትና ለወሮች ፤
ወለዐመታት ፤
ለዘመኖች ፤
ወለኢዮቤላት፤
ለአርባ ዘጠኙ ዘመናት ፤
ወለሁሉ ጊዜ ዓመታት ፤
በዓመት ለሚመላለሱ ሰዓቶች ሁሉ ምልክት ሊሆን ለሱባኤዎችና ለቀኖች ፀሐይን ፈጠረ ።።
ወይፍልጥ ማዕከለ ብርሃን ወማዕከለ ጽልመት ፤
በጨለማና በብርሃን መካከል ድንበር ሆኖ ይለይ ዘንድ ፤
ወለአጥአዮ ከመ ይጥአይ ሁሉ ዘይሠርፅ ወይልህቅ ዲበ ምድር፤
በምድር ላይ የሚበቅለው የሚያድገው ሁሉ ይድን ዘንድ ለማዳን ፀሐይን ፈጠረ ፤
ፎተ ዘንተ ዘመደ ገብረ በዕለት ራብዕት ፤
ባራተኛዪቱ ቀን በዕለተ ረቡዕ እነዚህን ሶስት ፍጥረታት ፈጠረ ።።
፲፮፤ ወበሐምስት (ሐሙስ) ዕለት ፈጠረ አናምርተ ዐበይተ ማዕከለ ቀላያተ ማያት ፤
ባምስተኛዪቱ ቀን በጥልቅ ውሃዎች መካከል ያሉ ታላላቆች ዓሣ አንበሪዎችን ፈጠረ ፤
እስመ ዝንቱ ኩሉ ተገብረ ቀዳሚ በዕደዊሁ ፤
ይህ ሁሉ መጀመሪያ በሥልጣኑ ተፈጥሯልና ፤
ኩሉ ዘሥጋ ወኩሉ ዘይትሐወስ ውስተ ማያት ፤
በውሀዎችም ውስጥ የሚመላለስ ፍጥረት ሁሉ ፤
ዓሣት ወኩሉ ዘይሠርር አዕዋፍ፤
የሚበሩ ወፎች ሁሉና ዓሣ ዎቹም ፤
ወኩሉ ዘመዶሙ ፤
ወገናቸውም ሁሉ ተፈጥሯልና ።።

፲፯፤ ወሠረቀ ፀሐይ ላዕሌሆሙ ለጥዒና ፤
ፀሐይም ሕይወት ሊሆናቸው በእነሳቸው ላይ ወጥ ቷልና ፤

ወላዕለ ኩሉ ዘሀሎ ውስተ ምድር ፤
በዚህ ዓለም በሚኖር ፍጥረትም ፤
ወኩሉ ዘይሠርፅ እምድር ፤

ከምድር በሚበቅለውም ሁሉ ላይ ፤
ወኩሉ ዕፀው ዘይፈሪ ፤
በሚያፈራውም ዕንጨት ሁሉ ላይ ፤

ወኩሎ ዘሥጋ ዘንተ ኩሎ ሠለስተ ዘመደ ገብረ አመ ዕለት ሐምስት፤
በሥጋዊ በደማዊ ሁሉ ላይ ወጥቷልና ባምስተኛዪቱ ቀን ሐሙስ እነዚህን ሦስቱን ፍጥረቶች ሁሉ ፈጠረ።

፲፯፤ ወበሳድስት ዕለት ገብረ ኩሎ አራዊተ ምድር ወኩሎ እንስሳ ፤

በስድስተኛይቱም ቀን እንስሳትንና አራዊትን ሁሉ፤
ወኩሎ ዘይትሐወስ ውስተ ምድር ፤
በምድር ላይ የሚመላለስ ሰውንም ሁሉ ፍጥረት ፈጠረ ፤

ምዕራፍ ፫

፩፤ ወእምድኅረዝ ኩሉ ገብረ ሰብአ አሐደ ፤
ይህንን ሁሉ ፍጥረት ከፈጠረ በኋላ አንድ ሰው አዳምን ፈጠረ ፤
ብእሴ ወብእሲተ ገብሮሙ ፤
ወንድና ሴት አድርጎ ፈጠራቸው ፤
ወአሥለጦ ለሰብእ ላዕለ ኩሉ ዘዲበ ምድር ወዘውስተ አብሕርት ወዲበ ዘይሠርር፤
በባሕር ውስጥ ባለው ፍጥረትና በምድር ላይ ባለው ፍጥረት ሁሉ ላይ አዳምና ሔዋንን አሠለጣናቸው ፤
ወዲበ አራዊት ወዲበ እንስሳ ፤
በአራዊት በአዕዋፍ ላይ፤
ወዲበ ኩሉ ዘይትሐወስ ዲበ ምድር ወላዕለ ኩሉ ምድር ፤
በዚህ ዓለም በሚመላለሰው ፍጥረት ሁሉና በዚህ ዓለም በሚመላለሰው በዓለሙም ሁሉ ፤
ወዲበ ዝ ኩሉ አሥለጦ ፤
በዚህ ሁሉ ላይ አሰለጠነው፤

ወ፬ተ ዘንተ ዘመደ ገብረ በዕለት ሳድስት ፤
በስድስተኛዪቱ ቀን፤ ዓርብ ፬ቱን ስነ ፍጥረት ፈጠረ ።

፪፤ ወኮነ ኩሉ ፳ ወ፪ተ ዘመደ፤
የተፈጠረው ፍጥረት ሁሉም ሐያ ሁለት ስነ ፍጥረት ሆነ ፤
ወፈጸመ ኩሎ ግብሮ በዕለት ሳድስት ፤
በስድስተኛዪቱ ቀን ዓርብ ሥራውን ሁሉ ሠርቶ ጨረሰ ፤
ወኮሉ ዘበሰማይ ወዘበምድር ፤
በምድርና በሰማይ ፤
ውስተ አብሕርት ወውስተ ቀላያት ፤
በጥልቁና በባሕሩ ውስጥ ፤
ወውስተ ብርሃን ወውስተ ጽልመት ወውስተ ኩሉ ፤
በጨለማና በብርሃንም መካከል በዓለምም ላይ ያለውን ፍጥረት ሁሉ ፈጥሮ ጨረሰ ።

፫፤ ወወሀበነ ትእምርተ ዓቢየ ዕለተ ሰንበታት ከመ ንኩን እንዘ ንገብር ሰዱስ ዕለተ ግብረ ወናሰንብት በሳብዕት ዕለት እምኩሉ ግብር ፤
ስድስት ቀን ሥራ ሠርተን በሰባተኛዪቱ ቀን ከሥራችን ሁሉ ዕረፍት የምናደርግ እንሆን ዘንድ ታላቅ በዓል የምትሆን ሰባተኛዪቱን ቀን ቀዳሚትን ብዙ ምልክት አድርጎ ሰጠን ።

፬፤ ኩሎሙ መላእክተ ገጽ ፤
ባለሚልነት ያላቸው በባለ ሚልነት ያሉ መላእክት ሁሉ ስድስት ቀን ሥራ ሠርተን እንውል ዘንድ በሰባተኛው ቀዳሚትን እና ክብር ዘንድ ሰጠን ይላሉ ፤
ወኮሎሙ መላእክተ ቅዳሴ ፪ቱ ዘመድ ዐበይት ዘንተ ይቤለነ ናሰንብት ምስሌሁ በሰማይ ወበምድር ፤

የሚያመሰግኑ ሁለቱ መገ ብተ ቅዳሴ መላእክትና ደቂቀ አዳም ከሱ ጋራ እና ክብር ፤ ዕረፍት እናደርግ ዘንድ ይሽን አለን ይላሉ ።

፭፤ ወይቤለነ ናሁ አነ እፈልጥ ሊተ ሕዝበ እማዕከለ አሕዛብ ፤
እነሆ እኔ ከአሕዛብ መካከል ወገኖቼን እለያቸዋለሁ፤

ወያሰነብቱ እመ·ንቱኒ ፣
እነሳቸውም በዓሉን ያከብራሉ ፤
ወእቁድስ ሊተ ሕዝበ ወእባ
ርከመ ፣
የእኔ ወገን ሊሆኑ እለያቸ
ዋለሁ ፤
በከመ ቀድስክዋ ለዕለተ ሰንበት
ወእቁድሶሙ ሊተ ፣
ዕለተ ሰንበት ቀዳሚትንም
እንደለየኋት እንዳከበርኋት
አከብራቸዋለሁ ::

፮፤ ወከመዝ እባርኮሙ ወይከ
ውኑኒ ሕዝብየ ፤
እንዲህ አከብራቸዋለሁ ወገ
ኖቼም ይሆናሉ ፣
ወእነ እከውኖሙ አምላክ ፤
እኔም አባት እሆናቸዋለሁ ፤
ወንረይክም ለዘርዓ ያዕቆብ
በኵሉ እምዘርኢኩ ፣
ካየሁት ወገን ይልቅ በሁሉ
የያዕቆብን ልጅ መረጥ
ኩት፤ ወጸሐፍክም ሊተ ልደ
በኵረ ፤
ለእኔ የበህር ልጅ አድርጌ
ጻፍኩት ፣
ወቀደስክም ሊተ ለዓለመ
ዓለም፣
ለዘለዓለምም አከበርኩት ::

፯፤ ወዕለታተ ሰንበታት እኤም
ሮሙ ከመ ያሰንብቱ ባቲ
እምኵሉ ግብር ፤
ከሥራው ሁሉ ያርፉባት
ዘንድ በሰባኤ የምትቈጠር
ቀዳሚትን ለእሥራኤል
አመለክታቸዋለሁ ፣
ወገብረ ቦቱ ትእምርተ ከማሁ
በዘያሰነብቱ ባቲ ፣
በሚያርፉባት ፤ በዓል በሚ
ያከብሩባት ገንዘብ ይኸን
ምልክት አደረገ ::

፰፤ ወእመ·ንቱኒ ምስሌነ
በሳብዕት ዕለት ለበሊዕ መለስትይ
ወለባርኮ ለዘፈጠረ ኵሉ በከመ
ባረከ ወቀደሰ ሎቱ ሕዝበ
ዘያስተርኢ እምኵሉ አሕዛብ
ከመ ያሰንብቱ ኅቡረ ምስሌነ ፤
ምስለና ምስሌነ አንድ
ወገን፤ በሰባተኛዪቱ ቀን
እሥራኤል ከኛ ከመላእክት
ጋራ አንድነት ያከብሩ
ያርፉበት ዘንድ ገብረ ይላል
መልአከ ገጽ ::

፱፤ ወገብረ እግዚአብሔር በቅድሜሁ ፈቃዳቲሁ ይዕርግ መዓዛ ሠናይ ዘይትቄከፍ ቅድሜሁ ኵሎ መዋዕለ ፤
ቅድሜሁና ቅድሜሁ አንድ ወገን ፤ በዘመኑ ሁሉ በፊቱ በኅ መዓዛ አድርጎ የሚቀበለው መሥዋዕት ያርግ ዘንድ በፊቱ በኅ መዓዛ ሆኖ ሊደርስ መሥዋዕትን ሠዋ ፤
፭ወ፪ቱ አርዕስተ ሰብእ እምአዳም እስከኔሁ ፤
ከአዳም ጀምሮ እስከ ያዕቆብ የተነሡ የነበሩ ያሉ አበው ሃያ ሁለት ናቸው ፤
ወ፭ወ፪ኤቱ ዘመደ ግብር ተገብረ እስከ ዕለት ሳብዕት ፤
እስከ ሰባተኛዪቱ ቀን እስከ ቀዳሚት ሐያሁለት ስነ ፍጥረት ተፈጠረ ፤
ዝንቱ ቡሩክ ወቅዱስ ሰንበቱ ፤
ይህም ቀዳሚት ልዩ ክቡር በዓል ነው ፤
ወውእቱኒ ቡሩክ ወቅዱስ ፤
ያም እስራኤል ልዩ ክቡር ነው ::
፲፤ ወዝንቱ ምስለ ዝንቱ ኮነ ለቅዳሴ ወለበረከት ፤
ይህ ከዚህ ጋር ለምስጋና ለበረከት ሆነ በሰንበት ከያዕቆብ ጋራ ለምስጋና ሆነ ፤
ወተውህቦ ለዝንቱ ከመ ይኩኑ ኵሎ መዋዕለ ቡረካነ ወቅዱሳነ፤
ሰባተኛይቱን ቀን ሰንበትን ቀድሞ ለይቶ እንዳከበራት በሚያከብሩበት ዘመን ሁሉ ልጆቹ የከበሩ የተለዩ ይሆኑ ዘንድ ለያዕቆብ ዕለተ ሰንበት ተሰጠው ፤
ዘስምዕ ፤
ኢታምልክን ፤
ወዘሕግ ፤
ዘጠኙን ሕግጋት የሚጠብቁ ይሆኑ ዘንድ ፤
ቀዳሚ በከመ ተቀደሰ ወተባረከ ዕለተ ሰንበት፤
ቀድሞ እንደ ተለየ ተለይቶ እንደከበረ እሥራኤል ዘመኑን ሁሉ በዘመኑ ሁሉ ቀኑን ሁሉ በቀኑ ሁሉ የተለዩ የከበሩ ይሆኑ ዘንድ ዕለተ ሰንበትን ሰጠው ::

ጉባኤ

፲፭፤ ወበሳብዕት ዕለት ፈጠረ ሰማየ ወምድረ ፤
በመጀመሪያዪቱ ሱባዔ ሰማይንና ምድርን ፈጠረ ፤
ወኵሎ ዘተፈጥረ በሰዱስ ዕለት፤

በስድስቱ ቀን የተፈጠረውንም ፍጥረት ሁሉ ፈጠረ ፤
ወወሀበ እግዚአብሔር ዕለተ በዓል ቅድስት ለኩሉ ምግባሩ ፤
እግዚአብሔር ለፍጥረቱ ሁሉ የከበረች በዓል የምት ደረግበት ቀን ቀዳሚትን ፈጠረ ፤
በእንተዝ አዘዘ በእንቲአሃ ኩሉ ዘይገብር ባቲ ኩሎ ግብረ ለይሙት ፤
ስለዚህ ነገር ሥራውን ሁሉ የሚሠራባት ሰው ሁሉ ይሞት ዘንድ አዘዘ ፤
ወዘኒ ያረኩሳ ሞተ ለይሙት ፤
ዘሰዓራ ሲል ነው የሻራትም ሰው ሁሉ ሞተ ሥጋ ሞተ ነፍስን ይሙት ፤
ወበሳብዕት ዕለት ፈጠረ እግዚአብሔር ሰማየ ወምድረ ፤
በመጀመሪያዪቱ ሱባኤ እሁድ እግዚአብሔር ሰማይና ምድርን ፈጠረ ፤
ወኩሉ ዘተፈጥረ በሰዱስ ዕለት፤
አክብሯት ዕረፋባት ብሎ ዕለተ በዓል የሚደረግባት ቀዳሚትን ለፍጥረቱ ሁሉ ሰጠ ፤
ወወሀበ እግዚአብሔር ዕለተ በዐል ቅድስት ለኩሉ ምግባሩ ፤
እግዚአብሔር ለፍጥረቱ ሁሉ የከበረች በዓል የምት ደረግበት ቀን ቀዳሚትን ፈጠረ ፤
በእንተዝ አዘዘ በእንቲሃ ፤ ኩሉ ዘይገብር ባቲ ኩሎ ግብረ ሰይ ሙት ፤
ያረኩሳ ሲል ነው ፤
ስለዚህ ነገር ሥራውን ሁሉ የሚሠራባት ሰው ሁሉ ይሞት ዘንድ አዘዘ ፤
ወዘኒ ያረኩሳ ሞተ ለይሙት ፤
ዘሠዓራ ሲል ነው የሻራትም ሰው ሁሉ ሞተ ሥጋ ሞተ ነፍስን ይሙት ፤

፲፪ ፤ ወአንተኒ አዝዝ ለደቂቀ እሥራኤል ፤
መልአከ ገጽ ሙሴን አንተም ሙሴ የእስራኤልን ልጆች እዘዛቸው ፤
ወይዕቀቡ ዛተ ዕለተ ፤
ይቺን ቀን ይጠብቁ ዘንድ ፤
ወከመ ይቀድስዋ ፤

ያከብሯትም ዘንድ አዝዘ ይለዋል መልአከ ገጽ ሙሴን ፤
ወከመ ኢይግበሩ ባቲ ኵሉ ግብረ ፤
ሥራውንም ሁሉ እንዳይሠሩባት ፤
ወከመ ኢያርኵስዋ አስመ ቅድስት ይእቲ እምኵሉ መዋዕል ፤
ኢይሥዓርዋ ሲል ነው ፤ ከዕለታት ሁሉ እርሷ የከበረች ናትና እንዳይሸሯት ይችን ቀን ይጠብቁ ::

፲፫ ፤ ወኵሉ ዘያቄምና ሞተ ለይሙት ፤

የሚሸራትም ሰው ሁሉ ሞትን ይሙት ፤

ወኵሉ ዘይገብር ባቲ ኵሉ ግብረ ሞተ ለይሙት ለዓለም ፤
ሥራውን የሚሠራባትም ሰው ሁሉ ለዘለዓለሙ ሞትን ይሙት ፤

ከመ ይዕቀቡ ደቂቀ እስራኤል ሣቱ ዕለተ በትውልዶሙ ፤
የእስራኤል ልጆች በትውልዳቸው ይህችን ቀን ይጠብቁ ዘንድ ፤
ወኢይሠረዉ እምድር ፤
ከምድርም እንዳይጠፉ ፤
አስመ ዕለት ቅድስት ይእቲ ወዕለት ቡርክት ይእቲ ፤
የተለየች የከበረች ቀን ናትና ፤

፲፬ ፤ ወኵሉ ሰብአ ዘየአቅባ ወዘያሰናብት ባቲ እምኵሉ ግብሩ ቅዱሰ ወብሩከ ይከውን በኵሉ መዋዕል ከማነ ፤

የሚጠብቃት የሚያከብራት ከሥራውም የሚያርፍባት ሰው ሁሉ ባለ በዘመኑ ሁሉ እንደ እኛ ክቡር ምስጉን ይሆናል ፤ ከማነ ማንሻ ፤ አንድም የሚያከብራት የሚጠብቃት ሁሉ ባለ በዘመኑ ሁሉ ከማነ እንደኛ ይሆናል ይላል መልአከ ገጽ ፤ ወገኖቹን መላእክትን ጨምሮ ከማነ አለ ::

፲፭ ፤ አይድዕ ወንግር ለደቂቀ እስራኤል ኵነኔሃ ለዛቲ ዕለት ፤
ሙሴ ! የዚችን ቀን ፍርዷን ለእስራኤል ልጆች ፈጽመህ ንገር ፤
ወያስንብቱ ባቲ ፤
በዓልን ያክብሩባት ፤

ወኢይጎድግዋ በስሕተተ ልቦሙ፤
በልቡናቸው ስሕተት እሷን ማክበር እንዳይተዉ ፤
ከመ ኢይኩኑ ለገቢረ ግብር ባቲ ዘኢይከውን ፤
የማይገባ ሥራን ለመሥራትም የተዘጋጁ እንዳይሆኑ ፤
ዘያስተርኢ ወዘኢያስተርኢ ለገቢር ባቲ ፈቃዶሙ ወከመ ያስተዳልዉ ባቲ ኵሉ ዘይትበላዕ ወዘይሰተይ ፤
የሚበላውን የሚጠጣውን ሁሉ ያዘጋጁ ዘንድ የሚታየውን የማይታየውን ሥራ ሁሉ በማይገባባት በሷ እንዳይሠሩ ::

፲፯፤ ወለቀዲሐ ማይ ፤
ውሀን ለመቅዳት ፤
ወለአውጽኦ ወለአብኦ ባቲ ኵሉ ዘይፀወር በአናቅጺሆሙ ፤
በዓደባባያቸው ሽክሙን ሁሉ በማግባት በማውጣት፤
ወዘኢያስተዳለዉ ሎሙ እሙንቱ በስዱስ ዕለት ኵሉ ግብረ ውስተ ማኅደሪሆሙ ፤
በዓደባባያቸው ያዘጋጁትን ሥራ ሁሉ የሚሸከሙትን ሽክሙን ሁሉ ለማውጣት ለማግባት ውሀ ለመቅዳት የተዘጋጁ ሁነው አይታዩ ::

፲፰፤ ወኢያውጽኡ ወኢያብኡ ምንተ በዛቲ ዕለት እምቤት ቤተ፤
በዚች ቀን ምንም ምን ከቤት ወደቤት አያውጡባት አያግቡባት ፤
እስመ ቅድስት ይእቲ ወቡርክት ይእቲ እምኵሉ ዕለተ ኢዮቤል ዘኢዮቤላውስት ባቲ ፤
ከኢዮቤል ውስጥ ያለ ኢዮቤል ከሚቆጠርባት ቀን ሁሉ ተለይታ የከበረች ናትና ፤
እስመ ባቲ አስንበትነ በስማያት ዘእንበለ ይትአመር ለኵሉ ዘሥጋ ለአስንብቶ ባቲ በምድር፤
በምድር ዕረፍት ያደርጉባት ዘንድ ለሥጋዊ ለደማዊ ሁሉ ሳይታወቅ እኛ በሰማይ ዕረፍት አደረግንባት::

፲፰፤ ወባረካ ፈጣሬ ኵሉ ፤ ሁሉን የፈጠረ እግዚአብ ሔር እኛ እንድናከብራት አክብሯታልና ፤ አንድም አከበራት ፤

ወኢቀደሰ ኵሎ አሕዛበ ለአለ ንብቶ ባቲ ዘእንበለ እስራኤል ባሕቲቱ ፤

ከእስራኤል ብቻ በቀር አሕ ዛብን ሁሉ አልመረጠም ፤ ሎቱ ለባሕቲቱ ወህበ ይብላዕ ወይስተይ ወለአለንብቶ ባቲ ዲበ ምድር ፤

በልቶ ጠጥቶ በምድር ዕረፍትን ያደርግባት ዘንድ ለእርሱ ለእስራኤል ብቻ ሰጠው ፤

፲፱፤ ወባረከ ፈጣሬ ኵሉ ፤ ዛተ ዕለተ ለበረከት ወለቅድሳት ወለስብሓት እምኵሉ መዋዕል ፤

ከቀን ሁሉ ተለይታ ለመከ በር ለማመስገኛ ልትሆን ይችን ቀን የፈጠረ እግዚአ ብሔር አከበራት ፤

ዝንቱ ሕግ ወስምዕ ተውህበ ለደቂቀ እሥራኤል ወሕግ ዘለ ዓለም ለትውልዶሙ ፤

ይህ ሕግ ይህ ሥርዓት ለእስራኤል ልጆች በዘመ ናቸው የዘለዓለም ሥርዓት ሆኖ ተሰጠ ።

ምዕራፍ ፬

፩፤ ወበሰዱስ መዋዕል ዘሰንበት ካልዕ አምጻእነ በቃለ እግዚአ ብሔር ኀበ አዳም ኵሉ አራዊተ ወኵሉ እንስሳ ወኵሉ አዕዋፈ ወኵሉ ዘይትሐወስ ውስተ ምድር ወኵሉ ዘይትሐወስ ውስተ ማይ በበዘመደመ· ወበበአምሳሎመ· ፤

በእግዚአብሔር ቃል ታዘን እንስሳትን ሁሉና አራዊትን ሁሉ በዚህ ዓለም የሚመ ላለሰውን ፍጥረት ሁሉ በየወገናቸው በየመልካቸው በሁለተኛው ሱባኤ በስድስ ተኛው ቀን ወደ አዳም አመጣን ይላሉ መላእክት።

፪፤ ወአራዊተ በቀዳሚት ዕለት፤ ሰዱስ ዕለተ ያለውን ይተረ ትራል ፤ በመጀመሪያዪቱ ቀን አራ ዊትን ፤

ወእንስሳ በሣኒታ ዕለት ፤
በሁለተኛይቱ ቀን እንስሳ
ትን ፤
ወአዕዋፈ በሣልስት ዕለት ፤
በሦስተኛዪቱ ቀን ወፎችን፤
ወኵሉ ዘይትሐወስ ዲበ ምድር
በዕለት ራብዕት ፤
በአራተኛው ቀን ረቡዕ በም
ድር የሚመላለሰውን ፍጥ
ረት ሁሉ ፤
ወኵሉ ዘይተሐወስ ውስተ ማይ
በዕለት ሐምስት ፤
በአምስተኛዪቱ ቀን በውሀ
ውስጥ የሚመላለሰውን ፍጥ
ረትሁሉ አመጣን ፤
ወሰመዮሙ አዳም ለኵሉሙ
በበአስማቲሆሙ ፤
አዳምም በየስማቸው ሁሉ
ንም ጠራቸው ፤
ወበከመ ጸውዖሙ ከማሁ ኮነ
ስሞሙ ፤ ስማቸውም አዳም
እንዳወጣላቸው እንደዚያው
ሆነ ::

፫፤ ወበሐምስ እላ መዋዕል
ሀለወ አዳም እንዘ ይሬኢ ዘንተ
ኵሉ ተባዕተ ወአንስተ ፤
በእነዚህ በአምስቱ ቀኖች
አዳም ይህን ሁሉ ፍጥረት
በምድር ያለውን ፍጥረት
ሁሉ ሴትና ወንድ ሆነው
ያይ ነበር ፤
ወኵሉ ዘመደ ዘበምድር ፤
በምድር ያለውን ወገንንም
ሁሉ ያይ ነበር ፤
ወውእቱሰ ሀሎ ባሕቲቱ ፤
እሱ ግን ብቻውን ነበር ፤
ወአልቦ ዘረከበ ሎቱ ዘይረድኦ
ዘከማሁ ፤
እንደርሱ ያለ ረዳትንም
ለእርሱ ያገኘው ማግኘት
የለም ፤

፬፤ ወይቤለነ እግዚአብሔር
ለነ፤
እግዚአብሔርም ለእኛ ነገ
ረን ፤
አኮ ሠናይ የሀሉ ብእሲ ባሕ
ቲቱ፤
አዳም ብቻውን ይኖር ዘንድ
አገባብ አይደለም አለ ፤
አላ ንግበር ሎቱ መርድኦ ዘከ
ማሁ ፤
እንደ እርሱ ያለ ረዳት እን
ፍጠርለት እንጂ ፤
ወወደየ እግዚአብሔር አምላክ
ሕድመተ ላዕሌሁ ወኖመ ፤
ፈጣሪአችን እግዚአብሔር
በአዳም እንቅልፍን አመ
ጣበት እሱም ተኛ ::

፫፤ ወነሥኣ ለብእሲት እማዕ
ከለ አዕፅምቲሁ አፅመ አሐደ ፤
ከአጥንቶቹ መካከል አንድ
አጥንትን አንሥቶ ሔዋንን
ፈጠራት ፤
ወይእቲ ገቦ ፍጥረታ ለብእሲት
ማዕከለ አዕፅምቲሁ ፤
የዚችም የሔዋን መፈጠሯ
ከአጥንቶቹ መካከል ነው ፤
ወሐነፀ ሥጋ ህየንቴሃ ፤
ስለ እርስዋም ፈንታ
ሥጋን መላ ፤
ወሐነፀ ብእሲተ
ሰው አደ ረጋት ፤
ወአንቅሖ ለአዳም እምንዋሙ ፤
አዳምንም ከእንቅልፉ አነ
ቃው ::

፮፤ ወነቂሖ አዳም ተንሥአ
በሳድስት ዕለት ወአምጽኣ ኀቤሁ
ለብእሲት ፤
አዳምም በስድስተኛዪቱ ቀን
ከእንቅልፉ በተነሣ ጊዜ ወደ
እርሱ አመጣት ፤
ወአአመራ ፤
አወቃት ፤
ወይቤላ ዛቲ አዕም እምአዕፅ
ምትየ ወሥጋ እምሥጋየ ፤
አዳምም ከእኔ ከባሏ ተገኝ
ታለችና ይህቺ የአጥንቴ
ፍላጭ የሥጋዬ ቁራጭ
ናት ፤
ዛቲ ትሰመይ ብእሲትየ ፤
ሚስት ትሁነኝ አለ ፤
እስመ እምነ ብእሲሃ ተነሥ
አት፣
ከእኔ ከባሏ ተገኝታለችና ፤
በእንተዝ ይከውኑ ብእሲ ወብ
እሲት አሐደ ሥጋ ፤
ስለዚህ ነገር ባልና ሚስት
አንድ አካልን ይሆናሉ ::

፯፤ ወበእንተዝ የኀድግ ብእሲ
አባሁ ወእሞ ወይፃመር ምስለ
ብእሲቱ ወይከውኑ አሐደ
ሥጋ፤
ስለዚህም ነገር ሰው እናቱ
ንና አባቱን ትቶ ሚስቱን
ይከተላል ፤ ከእርሷም ጋር
አንድ ይሆናል ፤ ሁለቱም
አንድ አካል ይሆናሉ ::

፰፤ ወበሳብዕት ዕለት ቀዳሚት
ተፈጥረ አዳም ፤
በመጀመሪያዪቱ ሱባኤ
አዳም ተፈጠረ ፤
ወገቦ ብእሲቱ ወበሳብዕት
ካልዕት አርአዮ ሎቱ ኪያሃ ፤
በሁለተኛይቱም ሱባኤ
ሄዋንን ፈጥሮ በሳምንት
ዓርብ አሳየው ፤

ወበእንተ ዝንቱ ተውህበ ትእዛዝ ለአቄበ ሰቡዕ መዋዕል ለተባዕት ወለአንስት ፪ተ ሰቡዓ መዋዕለ ውስተ ርኩሰን ፤

ስለአደፋቸው ወንድ ቢወ ለድ አንድ ሱባዔ ፤ ሴት ብትወለድ ሁለት ሱባዔ ለመጠበቅ ተሰጠ ፤ ሱባዔ ያለው ሰባቱን ቀን ነው ።።

፴፤ ወእምድኅረ ተፈጸመ ለአ ዳም ፸ መዋዕል በምድር ኀበ ተፈጥረ አባዕናሁ ውስተ ገነተ ኤዶም ከመ ይትቀነያ ለምድረ ኤዶም ወይዕቀባ ፤

አዳም በተፈጠረበት ምድር ዐርባው ቀን ከተፈጸመ በኋላ ያርማት ይኰተኵ ታት ዘንድ ወደ ገነት አገ ባነው ይላሉ መላእክት ፤

ወለብእሲቱኒ አባዕናሃ በ፹ መዋዕል ፤

ሚስቱን ሔዋንንም በሰማ ንያ ቀን ወደ ገነት አገባ ናት።።

፴፩፤ ወእምድኅረ ዝንቱ ቦአት ውስተ ገነተ ኤዶም ፤

ከዚህ በኋላ ዔደም ወደም ትባል ገነት ገባች ፤

ወበእንተ ዝንቱ ተጽሕፈ ትእዛዝ ውስተ ጽላተ ሰማይ ለእንተ ትወልድ ለእመ ተባዕተ ወለደት ሰቡዓ መዋዕለ ትነብር ውስተ ርኩሳ በከመ ሰቡዕ ቀዳሚ መዋዕል ፤

ስለዚህ ነገር ይህ ዓለም ከተፈጠረ በኋላ አዳም ሳይፈጠር ሰባት ቀን ቄይቶ ተፈጥሮ ነበርና እንደሱ ወንድ ብትወልድ እስክትነጻ ሰባት ቀን ትቀመጥ ፤

፹ መዋዕለ ወሠሉሰ ዕለተ ትነብር ውስተ ደመ ንጽሓ ፤

ከደሟ መንጻት የሚያሻት ስለሆነ ሠላሳ ሦስት ቀን ትቀመጥ ።።

፴፪፤ ወኵሉ ቅዱስ ኢትግ ሥሥ ወውስተ መቅደስ ኢትባእ እስከ ትፈጽም ዘንተ መዋዕለ ዘበተባዕት ፤

ንዋየ ቅድሳቱን አትንካ ፤

በወንድ ልጅ የታዘዘውን ይህን ቀን አስክትፈጽም ድረስ ወደ ቤተ መቅደስም እንዳትገባ ሥርዓት ተጻፈ፤

፹፪ኤ ሰቡዓተ መዋዕለ ዘበ አንስት ፤

በወንድ ያለው ያንዱ ሱባዔ መዋዕልና ፤ ዘንተ መዋዕለ አንድ ወገን ነው ፤

በሴትም ያለ ሁለቱን ሱባዔ እስክትፈጽም ድረስ ትቀመጥ ፤
በከመ ፪ኤ ሰቡዓት ቀዳምያት በርኩሳ ፤
ይህ ዓለም ከተፈጠረ በኋላ ሄዋን ሳትፈጠር ሁለት ሱባዔ ሰንብታ ተፈጥራ ነበርና እንደተፈጠረች ፤ ፪ኤ ሰቡዓተ ዘበአንስት አለ ፤
ወኟሳ መዋዕለ ወሰዱሰ ዕለተ ትነብር በደመ ንጽሓ ፤
ከግዳጇ መንጻት የሚያሻት ስለሆነ ስሳ ስድስት ቀን ትቀመጥ ፤
ወይከውና ኩሉን ፹መዋዕለ ፤
ሁሉም ሰማንያ ቀን ይሆናሉ ፤

፲፪፤ ወፈጸማ አላንተ ፹ መዋዕለ አባዕናሃ ውስተ ኤዶም ፤
እነዚህን ሰማንያ ቀኖች ከጨረሰች በኋላ ወደ ገነት አገባናት ፤
እስመ ቅድስት ይእቲ ምድረ ኤዶም ውስተ ኩላ ምድር ፤
ገነት ከዓለመ ሁሉ የከበረች ናትና ፤
ወኵሉ ዕፅ ዘትኩል ውስቴታ ቅዱስ ፤
በውስጧም የበቀለው ዕን ጨት ሁሉ የከበረ ነው ::

፲፫፤ ወበእንተዝ ተሠርዐ ለእ ንተ ትወልድ ተባዕተ ወአንስተ፤
ስለዚህ ነገር ወንድና ሴት ለምትወልድ ሴት በእነዚህ ቀኖች ሥርዓት ተሠራ ፤
ፍትሐን በእማንቱ መዋዕል ኩሎ ቅዱሰ ኢትልክፍ ፤
እነዚህ ቀኖች እስኪፈጸሙ ድረስ ንዋየ ቅድሳትን ሁሉ አትንካ ፤
ወውስተ መቅደስ ኢትባዕ እስከ አመ ይትፈጸማ እላንቱ መዋዕል ለተባዕት ወለአንስት ፤
ለሴት ልጅና ለወንድ ልጅ የታዘዙ እነዚህ ቀኖች እስኪፈጸሙ ድረስ ንዋየ ቅድሳቱን ሁሉ አትንካ ፤
ወደመቅደስም አትግባ ፤
ወዝንቱ ሕግ ወስምዕ ዘተጽሕፈ ለእሥራኤል ይዕቀቡ ኩሎ መዋዕለ ፤
ባለ በዘመኑ ሁሉ ይጠብቁ ዘንድ ለእስራኤል የተጻፈው ሥርዓት ይህ ነው::

፲፬፤ ወበሱባዔ ቀዳማዊ ዘኤዮ ቤልዩ ቀዳሚ ሀለዉ አዳም ወብእሲቱ ፷ተ ዓመተ ውስተ ገነተ ኤደም እንዘ ይትቀነዩ ወየዓቅቡ ሀገረ ፤

በመጀመሪያው ሱባዔ በመ ጀመሪያው ኢዮቤልዩ ሚስ ቱና አዳም ሰባት ዓመት በገነት ሲገዙ ሕጉንም ሲጠ ብቁ ኖሩ ፤

ወምግባረ ኩሎ ወሀብናሁ ፤

ሥራን ተግባረ እድን አስተ ማርነው ፤ አንድም አቁ ጣሮ አስተማርነው ፤

ወሀሎነ እንዘ ንሜህር ገቢሮተ ኩሉ ዘያስተርኢ ለቅኔ ፤

ለማገልገል ለመገዛት ሁሉን ለመሥራት ስናስተምር ነበርን ይላሉ መላእክት እያረመ እየኰተኰተ ተቀ መጠ ፤

ወሀሎ አዳም እንዘ ይትቀነይ ፤

እሱም ሲያገለግል ኖረ ፤

፲፭፤ ወውእቱሰ ዕራቆ ፤

እሱ ግን ራቁቱን ነበር ፤

ወኢየአምር ፤

እራቁቱን እን ደሆነ አያው ቅም ነበር ፤

ወየዓቅብ ገነተ እምአዕዋፍ ወእ ምአራዊት ወእምእንስሳ ፤

ተክልንም ከአራዊትና ከወ ፍች ከእንስሳትም እንዳ ይበሉ ከነዚህ ሁሉ ይጠ ብቅ ነበር ፤

፲፮፤ ወያስተጋብእ ፍሬሁ ወይ በልዕ ፤

ፍሬውንም ለቅሞ ይበላ ነበር ፤

ወያነብር ትራፍ ሎቱ ወለብ እሲቱ ፤

ለሱም ለሚስቱም በልቶ የተረፈውን ያኖር ነበር ፤

ወያነብር ዘይትዓቀብ ፤

የሚጠብቀውንም ያኖር ነበር ፤

ወሐሊቆ ፍጻሜሁ ለ፷ቱ ዓመት እስ ፈጸመ በሀየ ፷ተ ዓመተ ጥንቁቀ ፤

ፈጽሞ ጠንቅቆ ፷ቱን ዘመን በገነት የፈጸማቸው የሰባቱ ዓመት ፍጻሜ ካለቀ በኋላ ::

፲፯፤ ወበካልዕ ወርኀ አመ ዐሡሩ ወስብዑ መጽአ አርዌ ምድር ወቀርበ ኀበ ብእሲት ፤

በሁለተኛው ወር ሁለተኛው ወር በባተ በግንቦት በአስራ ለባተኛው ቀን እባብ መጣ ፤
ወቀርበ ኀበ ብእሲት ፤
ወደ ሄዋን ቀረበ ፤
ወይቤላ አርዌ ምድር ለብእሲት፤

በምድር ላይ የሚሔድ እባ ብም ሄዋንን እንዲህ አላት፤

እምኵሉ ፍሬ ዕፀው ዘውስተ ገነት አዘዘክሙ እግዚአብሔር እንዘ ይብል ኢትብልዑ እም ኔሁ፤

በገነት ካሉ የእንጨቶች ፍሬ ሁሉ እግዚአብሔር ከእርሱ አትብሉ ብሉ ያዘ ዛችሁ ምንድን ነው ? አላት ፤

፲፮፤ ወትቤሎ እምኵሉ ፍሬ ዕፅ ዘእማዕከለ ገነት ይቤለነ እግዚአብሔር ብልዑ ፤
እግዚአብሔር በገነት ካለ እንጨት ፍሬ ሁሉ ብሉ ፤
ወእምነ ኵሉ ፍሬ ዕፅ ዘእማ ዕከለ ገነት ይቤለነ ኢትብልዑ እምኔሁ ፤

በገነት መካከል ካለ ከዕፀ በለስ ፍሬ ግን አትብሉ ፤
ወኢትልክፍዎ ከመ ኢትመውቱ፤
እንዳትሞቱ በእጃችሁም አትንኩ አለን አለችው ::

፲፱፤ ወይቤላ አርዌ ምድር ለብእሲት አኮ ክመ ሞተ ዘትመውቱ ፤

በምድር ላይ የሚሔድ እባ ብም ሔዋንን እንዲህ አላት ፈጽሞ ሞትን የምትሞቱ አይደለም ፤

አላ እስመ የአምር እግዚአብሔር አመ ዕለተ ትብልዑ እምኔሁ ከመ ይትረኀዋ አዕይንቲክሙ ወትከውኑ ከመ አማልክት ፤

ከእርሱ በበላችሁበት ቀን ዓይነ ልቡናችሁ እንዲበራ አምላክም እንድትሆኑ ያው ቃልና ትሆናላችሁ ብሎ ነው እንጂ ፤

ወተአምሩ ሠናየ ወእኩየ ፤
ክፉውንና በጎውንም እንድ ታውቁ እግዚአብሔር ያው ቃልና ነው እንጂ ሞትን የምትሞቱ አይደለም አላት::

፳፤ ወርእየት ብእሲት ዕፀ ከመ አዳም ውእቱ ፤
ሔዋንም እንጨቱ ያማረ እንደሆነ አየች ፤
ወያሠምር ለዓይን ፤
ለማየትም ደስ የሚያሰኝ ፤
ወሠናይ ፍሬሁ ለበሊዕ ፤
ፍሬው ለመብላት ደስ የሚያሰኝ እንደሆነ አየች ባየችም ጊዜ ፤
ነሥአት እምኔሁ ወመተረት ፍሬሁ ወበልዐት ፤
ከርሱ ቆርጣ በላች ፤
ወከደነት ኃፍረታ በቍጽለ በለስ ዘቀዳሚ ፤
ሰውነቷንም መጀመሪያ በበቀለው በበለሱ ቅጠል ሸፈነች ፤
ወወሀበቶ ለአዳም ወበልዐ ውእቱኒ ፤
ለአዳምም ሰጠችው እሱም በላ ፤
ወተርጎዉ አዕይንቲሁ ፤
አይኖቹም አዩ ፤

ወርእየ ከመ ዕራቁ ውእቱ ፤
እሱም ራቁቱን እንደሆነ ባየ ጊዜ ፤
ወነሥአ ቈፅለ በለስ ወጠቀበ ወገብረ ሎቱ ሞራዓ ፤

መዋርዓም ይላል ፤ የበለስ ቅጠል አምጥቶ ዳኮ ጉልሻ አድርጎ ሰፍቶ ፤
ወከደነ ኃፍረቶ ፤
ሰውነቱን ሸፈነ ::

፳፩፤ ወረገሞ እግዚአብሔር ለአርዌ ምድር ፤
እግዚአብሔርም የምድር እባብን ረገመው ፤
ወተምዖ ለአዳም ወረገሞ ለዓለም ፤
አዳምንም ተቈጣው ለዘለዓለምም ፈረደበት ::

፳፪፤ ወለብእሲትኒ ተምዓ ወረገማ ለዓለም እስመ ሰምዓት ቃለ አርዌ ምድር ወበልዐት ፤

ሔዋንንም የምድር እባብ የነገራትን ነገር ሰምታ ዕፀ በለስን በልታለችና ፈረደባት ፤

ወይቤላ አብዝኖ አበዝኅ ኀዘንኪ ወፃዕረኪ ፤

ፃዕርሽን ገዐርሽን አበዛዋለሁ አላት ፤
ወበሐዘን ወፃዕር ለዲ ውሉደ ወንበ ምትኪ ይኩን ምግባዕኪ ፤

አዝነኽ ተክዘኽ ልጅን ውለጂ ከወለድኽም በኋላ መመለሻሽ ወደ ባልሽ ይሁን ፤
ወውእቱ ይኰንንኪ ፣
እርሱም ይግዛሽ አላት ::

፳፫፤ ወለአዳምኒ ይቤሎ እስመ ሰሚዕከ ቃለ ብእሲትከ ወበላዕከ እምውስተ ውእቱ ዕፅ ዘአዘዝኩከ ከመ ኢትብላዕ እምኔሁ ፤
አዳምንም የሚስትህን ነገር ሰምተህ ከእሱ እንዳትበላ ካዘዝኩህ ከዚያ ከዕፀ በለሱ በልተሃልና ፤
ወከመ ትዕቀብ ኪያሁ ፤
እርሱን ትጠብቅ ዘንድ ከአዘዝኩህ በልተሃልና ፤
ርግምተ ትኩን ምድር በእንቲአከ ፤
ምድር ስለ አንተ የተረገመች ትሁን ፤
አሥዋክ ወአሜኽላ ይብቍልከ ፤
እሾህ አሜኸላ ይብቀልብህ ፤
ወብላዕ ጎብስተከ በሐፈ ገጽከ ፤
ጥረህ ግረህ እንጀራህን ብላ አለው

እስከ አመ ትገብዕ ውስተ ምድር እንተ እምኔሃ ተነሣእከ ፤
ከእርሷ ወደ ተገኘህባት ወደ ምድር እስክትመለስ ድረስ ፤
እስመ ምድር አንተ ወውስተ ምድር ትገብእ ፤
አንተ ከምድር ተገኝተሃልና ወደ ምድርም ትመለሳ ለህና::

፳፬፤ ወገብረ ሎሙ እግዚእ ብሔር አልባሰ ዘማዕስ ወአል በሶሙ ፤
እግዚአብሔርም የቁርበት ልብስ አልብሶ ፤
ወፈነምሙ እምገነተ ኤደም ፤
ከገነት አስወጥቶ አሰናበታቸው ::

ምዕራፍ ፮

፩፤ ወበይእቲ ዕለት እንዘ ይወጽእ አዳም እምገነተ ኤደም አጠነ ለመዓዛ ሠናይ ፤
አዳም ከገነት ሲወጣ በዚያች ቀን በጐ መዓዛ አድርጐ ሊቀበልለት ፤
ዕጣነ ፤
ዕጣንን ፤
ወስሂነ ፤
ነጭ ዕጣን ፤
ወቀንአተ ፤

ቀናዓት የሚባል ሽቱ ፤
ወማየልብን ፤
ልባንጃ የሚባል ሽቶ ፤
ወሰንበልተ ፤
ስንኩል ፤ የሚባል ሽቱ ፤
በጽባሕ ምስለ ትንሣኤ ፀሐይ
አመ ዕለተ ከደነ ኃፍረቶ ፤
ምስለ ሥርቀተ ፀሐይ ሲል
ነው ፤ ኃፍረቱን በሰወረበት
ቀን ፀሐይ ሲወጣ ከፀሐይ
ጋራ አዳም ከገነት ሲወጣ
ይህንን ሁሉ አጥኖ ወጣ ፤
እነሆ አሁን ዛሬ ነገ ትቄ
ረጣለህ ትሰቀላለህ ያሉት
ሰው እጅ ነሥቶ ሰግዶ
እንዲወጣ እሱም አጥኖ
ወጣ ይላሉ ::

፱፤ ወበይእቲ ዕለት ተፈፅመ
አፈ ኩሉ አራዊት ወእንስሳ
ወዘአዕዋፍ ወዘያንሶሱ ውስተ
ባሕር ወየብስ ወዘይትሐወስ
እምኀቤሃ ፤
በዚያችም ቀን የእንሰሳትና
የአራዊት ሁሉ በዚህ ዓለም
የሚመላለሰው ፍጥረትና
የወፎች የሚንቀሳቀሰውም
ፍጥረት ሁሉ አፍ ባንድ
ቋንቋ በአንድ አንደበት
ከመናገር ተከለከለ ፤
እስመ ኩሎሙ ይትናገሩ ዝንቱ
ምስለ ዝንቱ አሐደ ልሳነ
ወአሐደ ከንፈረ ፤
ከዚህ አስቀድሞ አንዱ
ከአንዱ ጋር በአንድ ቋንቋ
ይነጋገሩ ነበርና ::

፲፤ ወፈነወ እግዚአብሔር
እምገነተ ኤዶም ኩሎ ዘሥጋ
ዘህሎ ውስተ ገነተ ኤዶም ፤
እግዚአብሔርም በኤዶም
ገነት የሚኖረውን ሥጋዊ
ደማዊ ፍጥረትን ሁሉ ከገ
ነት አስወጥቶ አሰናበተ ::

፲፩፤ ወተዘርዉ ኩሉ ዘሥጋ
በበዘመዶሙ ወበበፍጥረቶሙ
ውስተ መካን ካልዕ ዘተፈጥረ
ሎሙ ፤
ሥጋዊ ደማዊ ፍጥረት
ሁሉ በየተፈጥሮአቸውና
በየወገናቸው ወደ ተፈጠሩ
ላቸው ቦታዎች ተበተኑ ::

፲፪፤ ወለአዳም ባሕቲቱ ወሀቦ
ክዳነ ከመ ይክድን ኃፍረቶ
እምኩሉ አራዊት ወእንስሳ ፤
ለአዳም ብቻ ከእንስሳትና
ከአራዊት ሁሉ ተለይቶ
ሰውነቱን ይሠውር ዘንድ
ልብስን ሰጠው ፤

ወበእንተ ዝንቱ ተአዘዘ ውስተ ጽላት ላዕለ ኵሎሙ እለ የአምሩ ፍትሐ ሕግ ይክድኑ ኃፍረቶሙ ወኢይትከሠቱ ከመ አሕዛብ ይትከሠቱ ፤
ስለዚህ ነገር የሥርዓቱን ፍርድ በሚያውቁ ሰዎች ሁሉ አሕዛብ እንዲገለጡ እንዳይገለጡ ሰውነታቸውን ይሰውሩ ዘንድ በሰማይ ጽላት ተጻፈ ::

ጉባዔ

፮፤ ወአመ ሠርቀ ወርኀ ራብዕ፤
አራተኛው ወር ነሐሴ በባተ ጊዜ ፤
ወጽኡ አዳም ወብእሲቱ እምገነተ ኤደም ፤
አዳምና ሚስቱ ኤደም ከሚባል ገነት ወጡ ፤
ወኃደሩ ውስተ ምድረ ኤልዳ ውስተ ምድረ ፍጥረቶሙ ፤
ከተፈጠሩበት ቦታ ኤልዳ በሚባል ሀገር አደሩ ፤
ወሰመየ አዳም ስመ ብእሲቱ ሄዋ ፤
አዳም የሚስቱን ስም ሔዋን ብሎ ጠራት ፤
እመሕያዋን ማለት ነው ፤
ወኢኮኑ ምስለ ወልድ እስከ ቀዳሚ ኢዮቤልዩ ፤
እስከ መጀመሪያው ኢዮቤልዩ ልዩ ድረስ ልጅ አልወለዱም ነበር ::

፯፤ ወእምድኅረ ዝንቱ ነገር አእመራ ፤
ከዚህ በኋላ በግብር አወቃት ፤
ወውእቱሰ ይትገበራ ለምድር በከመ ተምህረ በገነተ ኤደም ፤
እሱ ግን ኤደም በምትባል ገነት ማረም መኰትኰት እንደተማረ ምድርን ያርሳት ይቆፍራት ነበር ::

፰፤ ወበሣልስ ሱባዔ ፤
በሶስተኛው ሱባዔ ፤
በካልዕ ኢዮቤልዩ ፤
በሁለተኛው ኢዮቤልዩ ፤
ወለደቶ ለቃየን ፤
ቃየንን ወለደችው ፤
ወበራብዕ ወለደቶ ለአቤል ፤
ባረተኛው ሱባዔ አቤልን ወለደችው ፤
ወበሐምስ ወለደታ ለአዋን ወለታ ፤
ባምስተኛው ሱባዔ ልጂ አዋንን ወለደቻት ::

፱፤ ወበቀዳሚሁ ለኢዮቤልዩ ሣልስ ቀተሎ ቃየን ለአቤል ፤

በሶስተኛው ኢዮቤልዩ መጀ
መሪያ ቃየን አቤልን ገደ
ለው ፤
እስመ ተወክፈ እምእዴሁ ቍር
ባነ ፣
እግዚአብሔር ከአቤል እጅ
መስዋዕቱን ተቀብሏልና ፣
ወእምዕደ ቃየንሰ ኢተወክፈ
መሥዋዕቶ ፤
ከቃየን እጅ ግን መሥዋ
ዕቱን አልተቀበለምና ፤
ወቀተሎ በገዳም ፣
በምድረ በዳ ገደለው ፤
ወጸርሐ ደሙ እምድር ውስተ
ሰማይ እንዘ ይበኪ በእንተ
ዘተቀትለ ፤
በግፍ ስለ ሞተ ደሙ
እየተካሰሰ ከምድር እስክ
ሰማይ ድረስ ጮኸ ::

፲ ፤ ወዘለፎ እግዚአብሔር ለቃ
የን በእንተ አቤል ፤
በግፍ ስለ ገደለው ስለ
አቤል እግዚአብሔር ቃየንን
ዘለፈው ፤
ወገብረ ሎቱ ኑኃ መዋዕል ዲበ
ምድር ፤
የቃየንን ዘመኑን አበዛለት ፣
በእንተ ደመ እኑሁ አቤል ፤
የወንድሙ የአቤልን ደም
በምድር ላይ ስለአፈሰሰ ፤
ወረገሞ ዲበ ምድር ፤
በዚህ ዓለም ረገመው ፤

፲፩ ፤ በእንተ ዝንቱ ተጽሕፈ
ውስተ ጽላተ ሰማይ ፤
ስለዚህ ነገር በሰሌዳ ሰማይ ፣
አንድም በመላእክት ልቡና
ተጽፎአል ፤
ርኵም ውእቱ ዘይዘብጥ ካልየ
በእከይ ፤
ስለዚህ ነገር ባልጀራውን
በክፉት የሚደበድብ ርኩም
ነው ፤
ወይቤሉ ኵሎሙ እለ ርእዩ ፤
ይህን ያዩ የሰሙ ሰዎችም
ሁሉ ፣
ርኵመ ለይኩን ፣
የተረገመ ይሁን አሉ ፤
ወሰብአ ዘርእየ ወኢነገረ ፣
አይቶ ያልተናገረ ሰውም
ርኩም ከማሁ ፤
እንደሱ የተረገመ ይሁን ::

፲፪ ፤ በእንተዝ ንሕነ መጻእነ
ናይድዕ ቅድመ እግዚአብሔር
አምላክነ ኵሎ ኃጢአተ ዘይ
ከውን ውስተ ሰማይ ወምድር ፤

ስለዚህ ነገር አንድነቱን ስለ አወቅን በሰማይ በምድር የሚደረገውን ኃጢአት ፤ አንድም በፀሐይ በጨረቃ በድንጋይ በእንጨት የሚደረገውን ኃጢአት በእግዚአ ብሔር ፊት እንናገር ዘንድ መጣነ አሉ ፤

ዘብርሃን ወዘጽልመት ወዘበ ኵሉ ፤

በብርሃን በጨለማ በሁሉም የሚደረገውን እንነግር ዘንድ መጣነ ፤

ወሀለዉ አዳም ወብእሲቱ እንዘ ይላህዉ በእንተ አቤል አርባዕተ ሱባዔ ዓመት ፤

ሱባዔ ዘመን ዓመት አለ ፤ አራቱ ሱባዔ ዘመን ሃያ ስምንት ዘመን ይሆናል ፤ መቶ ዘመንም አለቀሱ ይላል ፤ አዳምና ሔዋን ስለ አቤል አራት የዘመን ሱባዔ ሃያ ስምንት ዓመት ሲያለ ቅሱ ኖሩ ።

፲፫ ፤ ወበራብዕ ዓመት ዘሱባዔ ሐምስ እንዘ ይትፈጸም መዋዕለ ትካዞሙ ፤

በአራተኛው ዓመት በአምስ ተኛው ሱባዔ መዋዕለ ኃዘናቸው ሲፈጸም ፤

ይቤሎ መልአከ ገጽ ለአዳም አቤል ወልድከ ተሳለመ ዕፀዊሃ ለገነት ፤

ልጅህ አቤል በእደ እግዚአ ብሔር ለመያዝ በቃ ተጠቀመልህ አለው ፤

ተፈሥሐ ፤

ያን ጊዜ ደስ አለው ፤

ወእምዝ አእመራ አዳም ዳግመ ለብእሲቱ ፤

ከዚህ በኋላ ዳግመኛ አዳም ሔዋንን በግብር አወቃት ፤

ወወለደት ሎቱ ወልደ ፤

ወንድ ልጅን ወለደችለት አዳም ሴትን ዘመቆ ሠላሳ ዘመን ወልዶታል ፤ ይህ ሁለተ ኢዮቤልዩ አራት የዘመን ሱባዔ ሁኖ አራት ዘመን ይተርፋል ፤

ወሰመዮ ስሞ ሴት ፤

ስሙንም ሴት አለው ምትክ ማለት ነው ፤

እስመ ይቤ እግዚአብሔር አን ሥአ ለነ ዘርአ ውስተ ምድር ካልዐ ህየንተ አቤል ፤

ስለ አቤል ፈንታ እግዚአ ብሔር በዚህ ዓለም ሌላ ልጅ አስነሣልን ብሎአልና

ስመ·ን ሴት አለው ፤ የአ
ቤል ምትክ ማለት ነው ፤
እስመ ቀተሎ ቃየን ፤
ቃየን አቤልን ስለገደለው ::

፲፬፤ ወበሱባዔ ሳድስ ወለዳ
ለአዙራ ወለቱ ፤
በስድስተኛው ሱባዔ ልጁ
አዙራንን ወለዳት ፤
ወነሥኣ ቃየን ለአዋን እኅቱ
ሎቱ ብእሲተ ፤
ቃየንም እኅቱ አዋንን
ሚስት አድርጎ ወሰዳት ፤
ወወለደት ሎቱ ኤኖንሃ በፍጻሜ
ራብዕ ዘኢዮቤልዩ ፤
ባራተኛው ኢዮቤልዩ መጨ
ረሻ ኤኖንን ወለደችለት
ኢዮቤልውም ይላል ::

፲፭፤ ወበአሐዱ ዓመትዘሱባዔ
ቀዳሚ ዘሐምስ ኢዮቤልዩ ፤
በመጀመሪያው ሱባዔ በአ
ንድ ዓመት በአምስተኛው
ኢዮቤልዩ ፤
ተሐንጹ አብያት ውስተ ምድር፤
በዚህ ዓለም ቤቶች ተሠሩ፤
ከዚህ አስቀድሞ በዱር በገ
ደል ይኖሩ ነበር ፤
ወሐነጸ ቃየን ሀገረ ፤
ቃየንም ሀገር አቀና መን
ደር መነደረ ፤
ወሰመያ ስማ በስመ ወልዱ
ኤኖህ ፤
ስሚን በልጁ ስም ኤኖህ
ብሎ ጠራት ::

፲፮፤ ወአእመራ አዳም ለሔዋን
ብእሲቱ ፤
አዳም ሔዋን ሚስቱን
በግብረ ሥጋ አወቃት ፤
ወወለደት ዓዲ ፱ተ ደቂቀ ፤
ዳግመኛ ዘጠኝ ልጆችን
ወለደችለት ::

፲፯፤ ወበሱባዔ ሐምስ ዘሐምስ
ኢዮቤልዩ ፤
በአምስትኛው ሱባዔ በአም
ስተኛው ኢዮቤልዩ ፤
ነሥኣ ሴት ለአዙራ እኅቱ ሎቱ
ብእሲተ ፤
ሴት እኅቱ አዙራን ሚስት
ትሆነው ዘንድ ወሰዳት ::
፲፰፤ ወበራብዑ ወለደት ሎቱ
ሄኖስሃ ፤
ባራተኛው ዘመን ሄኖስን
ወለደችለት ፤
ወውእቱ ወጠነ ቀዳሚ ጸውዖ
ስመ እግዚአብሔር በዲበ
ምድር፤

በዚህ ዓለም የእግዚአብ ሔርን ስም መጥራት የጀ መረ እሱ ነው ፤ ሐተታው እንደ አሪት ዘፍጥረት ምዕ ራፍ ፬ ቁጥር ፳፮ ከአን ድምታ ፤ ሄኖስን በመቶ አምስት ዘመን ወልዶታል አገናኝቶ ቢቆጥሩት ሁለት መቶ ሠላሳ አምስት ይሆ ናል ፤ ይህ አራት ኢዮቤ ልዩ ሁኖ ሠላሳ ዘጠኝ ይቀ ራል ፤ ይህን በሱባዔ ቢገ ቡት አምስት ሱባዔ ሆኖ አራት ዘመን ይተርፋል ፤ አምስተኛው ኢዮቤልዩ ከተ ጀመረ ብሎ ሐምስ አለ ሱባዔውም ከተጀመረ ብሎ አምስት አለ ።።

፲፱፤ ወበሳብዕ ኢዮቤልዩ በሱ ባዔ ሣልስ ነሥአ ሄኖስ ኖአምሃ እኅቶ ሎቱ ብእሲተ ፤
በሰባተኛው ኢዮቤልዩ ፤
በሶስተኛው ሱባዔ ሄኖስ እኅቱ ኖአምንን ሚስት ልትሆነው ወሰዳት ፤
ወወለደት ሎቱ ወልደ ፤
ወንድ ልጅ ወለደችለት ፤
በሣልስ ዓመት ዘሐምስ ሱባዔ ፤
በሶስተኛው ዓመት ባምስተ ኛያው ሱባዔ ወለደችለት ፤
ሄኖስ ቃይናንን በዘጠና ዘመን ወልዶታል ፤
ቢያገናኙት ሶስት መቶ ሃያ አምስት ይሆናል፤ ይህ ስድ ስት ኢዮቤልዩ ሆኖ ሠላሳ አንድ ዘመን ይተርፋል ይኸንንም በሱባዔ ቢያገና ኙት አራት ሱባዔ ሁኖ ሶስት ዓመት ይተርፋል ፤ ዘሐምስ ሱባዔ ማለቱ በአ ምስተኛው ሱባኤ በሦስ ተኛው ዘመን ሲል ነው ፤
ወሰመዮ ስሞ ቃይናን ፤
ስሙንም ቃይናን አለው ፤

፳፤ ወበፍጻሜ ሳምን ኢዮቤልዩ ነሥአ ሎቱ ቃይናን ብእሲተ ሙአሊሊትሃ እኅቶ ሎቱ ብእ ሲተ ፤
በስምንተኛው ኢዮቤልዩ ፍጻሜ ሚስት ትሆነው ዘንድ ቃይናን እኅቱ ሙአ ሊሊትን ወሰደ ፤
ወወለደት ሎቱ ወልደ በታስዕ ኢዮቤልዩ በሱባዔ ቀዳሚ ወበሣ ልስ ዓመት በሱባዔሁ ለዝ ፤
በዘጠነኛው ኢዮቤልዩ በመ ጀመሪያው ሱባዔ በሦስ ተኛው ዓመት በዚህ ሱባዔ ልጅን ወለደችለት ፤
ወጸውዐ ስሞ መላልኤል ፤

ስሙንም መላልኤል አለው ፤ ቃይናን መላልኤልን በ፹ ዘመን ወልዶታል ካለፈው ጋራ ቢገጥሙት ሶስት መቶ ዘጠና አምስት ይሆ ናል ፤ ይህ ስምንት ኢዮቤ ልዩ ሁኖ ሶስት ዘመን ይተርፋል ፤ ታስእ ማለቱ ግን ከተጀመረ ብሎ ፤ ቀዳሚም ማለቱ ሦስተኛው ዘመን ከተጀመረ ብሎ ነው ።።

፳፩ ፤ ወበካልዕ ሱባዔ ዘዐሥር ኢዮቤልዩ ነሥአ ሎቱ መላል ኤል ብእሲተ ዲናሃ ወለተ በራክኤል ወለተ እኅተ አቡሁ ሎቱ ብእሲተ ፤

በአሥረኛው ኢዮቤልዩ በሁ ለተኛው ሱባዔ መላልኤል ያባቱን እኅት ልጅ ዲናን ሚስት ልትሆነው ወሰዳት ፤ ወወለደት ሎቱ ወልደ በሱባዔ ሣልስ ወበሳድስ ዓመቱ ፤ በስድስተኛው ዓመት በሦስ ተኛው ሱባዔ ወንድ ልጅ ወለደችለት ፤ ወጸውአ ስሞ ያሮድሃ ፤ ስሙን ያሬድ አለው ፤ ርደት ማለት ነው ፤ እስመ በመዋዕሊሁ ወረዱ መላእክተ እግዚአብሔር ውስተ ምድር እለ ተሰምዩ ትጉሃነ ፤ ትጉሃን የተባሉ ትጉሃን ይባሉ የነበሩ ደቂቀ ሴት ፤ በእሱ ዘመን ወደዚህ ዓለም ወርደዋልና ፤ ከመ ይመሐርምሙ ለደቂቀ ዕጓለ እምሕያው ይግበሩ ፍትሐ ወርትዐ በዲበ ምድር ፤ በዚህ ዓለም የቀና ሥራን ፤ ፍትሕን ርትዕን ያደርጉ ዘንድ ለደቂቀ ቃየል ሊአስ ተምሯቸው ፤ መላልኤል ያሬድን በስልሳ አምስት ዘመን ወልዶታል ቢያገናኙት አራት መቶ ስልሳ ይሆናል ፤ ይህ ዘጠኝ ኢዮቤልዩ ሆኖ አስራ ዘጠኝ ዘመን ይተርፋል ፤ ይህንንም በሱባዔ ቢገቡት ሁለት ሱባዔ ሆኖ አምስት ዘመን ይተርፋል ፤ በሱባዔ ሣልስ ማለቱ ግን ከተ ጀመረ ብሎ ነው ፤ በሣድስ ዓመቱም ማለቱ አምስተ ኛው ዘመን ሲፈጸም ስድስ ተኛው ሊጀመር ነውና ።።

፳፪፤ ወበአሥር ወአሐዱ ኢዮቤልዩ ነሥአ ሎቱ ያሮድ ብእሲተ ፤
ባስራ አንደኛው ኢዮቤልዩ ያሮድ ሚስት አገባ ፤
ወስማ ባረካ ወለተ ራሱየል ወለተ እኅተ አቡሁ ሎቱ ብእሲተ ፤
ስሟ ባረካ ይባላል ሚስት ትሆነው ዘንድ ያባቱ እኅት ልጅ የምትሆን የራሱየልን ልጅ ወሰደ ፣
በሱባዔ ራብዕ ዘኢዮቤልዩ ዝንቱ ወለደት ሎቱ ወልደ ፤
በዚህ ኢዮቤልዩ ባራተኛው ሱባዔ ወንድ ልጅ ወለደች ለት ፣ ያሬድ ሄኖክን በ፷፪ ሱባኤ ወልዶታል ፣ ቢያገ ናኙት አምስት መቶ ሃያ ሁለት ይሆናል አሥር ኢዮ ቤልዩ ሆኖ ሠላሳ ሁለት ይተርፋል ሠላሳ ሁለቱን በሱባዔ ቢገቡት አራት ሱባዔ ሆኖ አራት ዘመን ይተርፋል ፣ በሱባዔ ሐምስ ማለቱ ስለ ተጀመረ ብሎ ነው ፣
በሱባዔ ሐምስ በራብዕ ዓመት ዘኢዮቤልዩ ፤
በኢዮቤልዩ ውስጥ ባለ ባራተኛው ዓመት ባምስተኛው ሱባዔ ፣
ወጸውዓ እንከ ስሞ ሄኖክ ፣ ስሙንም ሄኖክ አለው ፣ ሄኖህ ሄኖስም ይላል ፣ ሄኖክ ማለት ተሐድሶ ማለት ነው ፤
ወውእቱ ቀዳሚ ተምህረ ፤ እሱ አስቀድሞ መጽሐፈ አበውን ተማረ ፤
ወትምህርተ ወጥበበ እምዕጓለ እመሕያው እምእለ ተወልዱ ዲበ ምድር ፤
በዚህ ዓለም ከተወለዱ ከአ ዳም ልጆች ይልቅ ትምህ ርትን ጥበብን ተማረ ፡፡
፳፫፤ ወጸሐፈ ተአምረ ሰማይ፤ የፀሐይ የጨረቃን ሥርዐት ጻፈ ፣
በከመ ሥርዐተ አውራኂሆሙ ውስተ መጽሐፍ፣
እንደሥርዓታቸው ሠላሳ ሠላሳው ቀን ወር እንዲባል ጻፈ ፤
ከመ ያእምሩ ዕጓለ እመሕያው ጊዜ ዓመታት ፤
ሰዎች ሁሉ ዓመቱ ሶስት መቶ ስልሳ አምስት ቀን እንደሆነ ያውቁ ዘንድ ጻፈ፤
በከመ ሥርዓታቲሆሙ ለለወር ኖሙ ፤
እንደ ሥርዐታቸው መጠን እየወራቸው የዘመኑን ጊዜ ያውቁ ዘንድ ፤

፩፩፤ ወውእቱ ቀዳሚ ጸሐፈ ፤
አስቀድሞ እሱ ጻፈ ፤
ቀዳሚ ሰምዐ ፤
አስቀድሞ እሱ ሰማ ፤
ወአስምዐ ለደቂቀ እጓለ እመሕ
ያው ውስተ ትዝምደ ምድር ፤
በዚህ ዓለም ለሚኖሩ
ለሰዎች አስተማረ ፤
ወሱባዔሆሙ ለኢዮቤላውስት
ውእቱ ነገረ ፤
የኢዮቤልዩም ቁጥራቸው
፶፱ እንደሆነ ፤
ወመዋዕለ ዓመታት አይድዐ ፤
ዓመቱ ሦስት መቶ ስልሳ
አምስት ቀን እንደሆነ
ተናገረ ፤
ወአውራኀተ ሠርዐ ፤
ዓመቱ አስራሁለት ወር
እንደሆነ ጻፈ ፤
ወሰንበታተ ዓመታት ነገረ ፤
ዓመቱ አምሳ ሁለት ሱባዔ
እንደሆነ ተናገረ ፤
በከመ አይጻዕናሁ ፤
እኛ እንደነገርነው ፤
ወዘኮነ ፤
የተደረገውን ፤
ወዘይከውን ፤
ከንግዲህ ወዲህ የሚደ
ረገውን ፤
ርእየ በራእየ ንዋሙ ዘከመ ይከ
ውን ዲበ ደቂቀ ዕጓለ እመሕ
ያው በትውልዶሙ ፤
በዘመናቸው በሰዎች ልጆች
ሁሉ ላይ የሚሆነውን በሕ
ልሙ አየ ፤
እስከ አመ ዕለተ ደይን ኩሉ
ርእየ ፤
እስከ ዕለተ ምጽአት የሚሆ
ነውን ሁሉ አይቶ አወቀ ::
፩፪፤ ወጸሐፎ ስምዐ ፤
ምስክር ሊሆነው ጻፈው ፤
ወአንበሮ ስምዐ በዲበ ምድር
ላዕለ ኩሉ ደቂቀ እጓለ እመ
ሕያው ፤
በሰዎች ልጆች ሁሉ ላይ
በዚህ ዓለም ምስክር ሊሆ
ነው አኖረው ፤
ወለትውልዶሙ ፤
ለልጆቻቸው ምስክር ይሆን
ዘንድ አኖረው::
፩፫፤ ወበ፲ወ፪ኛ ኢዮቤልዩ ወበ
ሳብዕ ሱባዔሁ ሎቱ ነሥአ
ብእሲተ ፤
ባሥራ ሁለተኛው ኢዮቤ
ልዩ በሰባተኛው ሱባዔ
ሚስት አገባ ፤
ወስማ እድኒ ፤
ስሟም እድኒ ይባላል ፤

ወለተ ዳንኤል ወለተ እጎተ አቡሁ ሎቱ ብእሲተ ፤

ሚስት ትሆነው ዘንድ ያባቱ እህት የዳንኤልን ልጅ ወሰደ ::

፳፯፤ ወበሳድስ ዓመቱ በሱባዔሁ ለዝ ፤

በዚህ ሱባዔ በስድስተኛው ዓመት ፤

ወለደት ሎቱ ወልደ ፤
ወንድ ልጅ ወለደችለት ፤
ወጸውአ ስሞ ማቱሳላ ፤

ስሙንም ማቱሳላ ብሎ ጠራ ፤ ማቱሳላ ማለት ሞት ተፈነወ ማለት ነው፤ ሄኖክ ማቱሳላን በስልሳ አምስት ዘመን ወልዶታል ቢያገናኙት አምስት መቶ ሰማንያ ሰባት ይሆናል ፤ አሥራ አንድ ኢዮቤልዩ ሆኖ ሰባት ይተርፋል ::

፳፰፤ ወሀሎ ሄኖክ እንከ ምስለ መላእክተ አምላክ ፮ተ ዘኢዮቤላውስት ዓመታት ፤

ስድስተ ዓመታተ ዘኢዮቤላ ውስት ቢል ይመች ነበር ፤

በኢዮቤልዩ ውስጥ ባሉ ስድስት ዓመታት አምላክ ከፈጠራቸው አምላክን ከሚአመሰግኑ ከመላእክተ ጽድቅ ጋራ ኖረ ፤

ወአርአይዎ መላእክት ኵሎ ዘውስተ ምድር ወዘበሰማያት ሥልጣኖ ለፀሐይ ወዘወርኀ ፤
ወዘከዋክብት ያለበት ነው፤ የሰማዩን የምድሩን ሁሉ የፀሐይን የጨረቃን የከዋክብትን ሥልጣን አሳዩት ::

፳፱፤ ወጸሐፈ ኵሎ ፤

ሁሉን ጻፈ ፤
ወአስምዐ ለትጉሃን ለእለ አበሱ ምስለ አዋልደ ሰብእ ፤

ትጉሃን ለተባሉ ትጉሃን ይባሉ ለነበሩ ኋላ ከቃየል ልጆች ጋራ ለበደሉ በኃጢአት አንድ ለሆኑ ደቂቀ ሴት ጻፈ ፤
እስመ አኃዙ እሉ ይደመሩ ከመ ይርኩሱ ምስለ አዋልደ ሰብእ ፤
እሊህ ደቀቀ ሴት ከደቂቀ ቃየል ልጆች ጋራ ይበላሹ ዘንድ ከነዚያ ጋር ይጋቡ ዘንድ ጀምረዋልና ፤

ወአስምዐ ሄኖክ ላዕለ ኩሎሙ፤
ሄኖክም በሁሉም ላይ
አዳኝባቸው ::

፴፤ ወተንሥአ ሄኖክ እማዕከለ
ደቂቀ ዕጓለ እመሕያው ፤
ሄኖክም ከደቂቀ ቃየል
መካከል ተነሣ ፤
ወወሰድናሁ ውስተ ገነተ ኤዶም
በዕበይ ወክብር ፤
በክብር በጌትነት ኤዶም
ወደሚባል ገነት አገባነው
ይላሉ መላእክት፤
ወናሁ ውእቱ በሀየ ይጽሕፍ
ደይነ ወኩነኔ ዘለዓለም ፤
በዚያም ሆኖ የዘለዓለም
ቅጣትንና ቁርጥ ፍርድን
ይጽፍ ጀመር ፤
ወኩሉ እከዮሙ ለደቂቀ ዕጓለ
እመሕያው ፤
የሰውን ሁሉ ኃጢአት
ይጽፍ ጀመር ::

፴፩፤ ወበእንቲአሁ አምጽአ
እግዚአብሔር ማየ አይኅ ዲበ
ኩሉ ምድረ ኤዶም ፤
በኃጢአታቸው ምክንያት
እግዚአብሔር በዓለሙ
ሁሉ ላይ የጥፋት ውሃን
አመጣ ፤

እስመ ተውህበ ሄኖክ ለት
እምርት ፤
እሱ ለምሳሌ ተሰጥቷልና፤
ወከመ ያስምዕ ለኩሉ ደቂቀ
ሰብእ ፤
ለሰዎች ልጆች ሁሉ ያዳኝ
ዘንድ ፤
ወከመ ይንግር ኩሉ ግብረ ትው
ልድ እስከ አመ ዕለተ ደይን ፤
ቁርጥ ፍርድ እስከ ሚፈረ
ድባት ቀን ድረስ የፍጥረ
ቱን ሁሉ ሥራ ይናገር
ዘንድ ::

፴፪፤ ወውእቱ አጠነ ምሴተ
ዕጣነ መቅደስ ዘይሠጠው
ቅድመ እግዚአብሔር በደብረ
ቀትር ፤
ምሴት ሠርክ ነው ፤
መቅደስ ደብር ቀራንዮ
ነው፤ ዋዕየ ፀሐይ በጸናበት
በቀራንዮ አጠነ በቀራንዮ
ይሰቀላል ሲል ፤ አንድም
በቀትር አጠነ፤ በቀትር ይሰ
ቀላል ሲል ፤ አንድም ቀት
ርን አልፎ በሠርክ አጠነ
በሠርክ ይቀበራል ሲል ፤
አንድም ቀርቀር ይላል
ደብረ ቀትር ማለት ነው ፤

እስመ አርባዕቱ መካን ዲበ ምድር ለእግዚአብሔር ፤
ለእግዚአብሔር በምድር አራት ቦታዎች አሉትና ገነተ ኤዶም ፤
አርባዕቱ ያለውን ይተረት ራል
ኤዶም ፤
ገነት ፤
ወደብረ ጽባሕ ፤
ደብረ ዘይት ፤
ወዝደብር ዘሀለውከ አንተ ውስ ቴቱ ፤
ይህ ዛሬ አንተ ያለህበት ቀራንዮ ፤
ወደብረ ሲና ፤
ደብረ ሲና እሊህ አራቱ አሉትና ይሉታል መላእክት ሄኖክን ፤
ወደብረ ጽዮን ዘይትቄደስ በፍ ጥረት ሐዲስ ለቅዳሴ ምድር ፤
ምድርን ለማንጻት ለመ ቀደስ ቀራንዮ ፤ ኢየሩሳ ሌም በመስቀል ይነጻል ::

፴፫፤ በእንተዝ ትትቄደስ ምድር እምኵሉ አበሳ ወእም ርኩስ በትውልደ ዓለም ፤
ደሙ ስለፈሰሰባት ፤ በዚህ ዓለም በነቢብ በገቢር ሰው ከሚሠራው ኃጢአት ምድር ትነፃለች ::

፴፬፤ ወበኢዮቤልዩ ዘውእቱ ዐሥር ወራብዕ ኢዮቤልዩ ነሥአ ማቱሳላ እድኒሃ ብእሲተ ወለተ እዝራኤል ወለተ እኅተ አቡሁ ብእሲተ ሎቱ ፤
ባሥራ አራተኛው ኢዮቤ ልዩ ማቱሳላ ሚስት ትሆ ነው ዘንድ ያባቱ የእኅት ልጅ የምትሆን የእዝራኤ ልን ልጅ እድኒን ወሰደ ::

፴፭፤ በሱባዔ ሳድስ በዓመት አሐዱ ዘውእቱ ዓመት ወለደ ወልደ ፤
በስድስተኛው ሱባዔ ባንድ ዓመት ወንድ ልጅ ወለደ ፤
ወፀውአ ስሞ ላሜህ ፤

ስሙን ላሜህ አለው ለም ንት ሊተ ዕረፍት ማለት ነው ፤ ማቱሳላ ላሜህን በሰማንያ ሰባት ዓመት ወልዶታል ቢያገናኙት ስድ ስት መቶ ሰብዓ አራት ዘመን ይሆናል ፤ ስድስቱ መቶ አስራሁለት ኢዮቤልዩ ሁኖ አሥራ ሁለት ዘመን ይተርፋል አስራ ሁለቱን ዘመን ከሰባ አራቱ ቢገ

ጥሙት ሰማንያ ስድስት ይሆናል ፤ ሰማንያ ስድስቱ አንድ ኢዮቤልዩ ሆኖ ሠላሳ ሰባት ዘመን ይተርፋል ፤ ሠላሳ ሰባቱ ዘመን አምስት ሱባዔ ሆኖ ሁለት ዘመን ይተርፋል ።።

፴፮፤ ወበዐሥር ወሐምስ ኢዮቤልዩ በሱባዔ ሣልስ ነሥአ ሎቱ ላሜህ ብእሲተ ፤
ባሥራ አምስተኛው ኢዮቤልዩ በሦስተኛው ሱባዔ ላሜህ ሚስት ልትሆነው ወሰደ ፤
ወስማ ቤቴናስ ፤
ስሟም ቤቴናስ ትባላለች ፤
ወለተ በራኪኤል ወለተ እኅተ አቡሁ ሎቱ ብእሲተ ፤
ሚስት ትሆነው ዘንድ የአባቱን እኅት የበራኪኤልን ልጅ ቤቴናስን ወሰደ።።

ምዕራፍ ፮

፩፤ ወበዝ ሱባዔ ወለደት ሎቱ ወልደ ፤
በዚህ ሱባዔ ወንድ ልጅ ወለደችለት ፤ ላሜህ ኖኅን በሰማንያ ሁለት ዘመን ወልዶታል ፤
ቢያገናኙት ሰባት መቶ ሃምሳ ስድስት ይሆናል ፤ ዐሥራ አራት ሱባዔ ሁኖ ሰባ ዘመን ይተርፋል ፤ ከሰባው አርባ ዘጠኝ ሲነ ሣለት ሃያ አንድ ዘመን ይቀራል ፤ ይህንም በሱባዔ ቢገቡት ሦስት ሱባዔ ይሆናል ፤
ወጸውኦ ስሞ ኖኅ ፤
ስሙን ኖኅ አለው ፤ ኖኅ ማለት ዕረፍት ፤ ትፍሥሕት ፤ ተረፍ ፤ ማለት ነው ፤
እንዘ ይብል ዘይናዝዘኒ እምኵሉ ግብርየ ፤
ከሥራዬ ሁሉ የሚያሳርፈኝ ይህ ነው ሲል ዕረፍት አለ ፤
ወእምኵሉ ኃዘንየ ፤
ከኃዘኔ ሁሉ የሚያረጋጋኝ ሲል ትፍሥሕት አለ ፤
ወእምድርኒ እንተ ረገማ እግዚአብሔር ፤
እግዚአብሔር ከረገማት ከፈረደባት ምድር ይቀራል ሲል ተረፍ አለ ።።

፪፤ ወበፍጻሜሁ ለዐሥር ወታ ለዕ ኢዮቤልዩ ፤
ባስራ ዘጠነኛው ኢዮቤልዩ መጨረሻ ፤